ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 014 መስከረም 14 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

## በሆሳዕና ከተማ የተጀመረው የኮሪደር ልማት በአንድ ወር ጊዜ ይጠናቀቃል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በሆሳዕና ከተማ የተጀመረው የ2 ነጥብ 6 ኪሎ ሜትር የኮሪደር ልማት ሥራ ከአንድ ወር በኋላ ተጠናቅቆ ለአገልግሎት እንደሚበቃ የከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ፡፡

የከተማው ከንቲባ አቶ ዳዊት ጡምደዶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከተማ አስተዳደሩ 200 ሚሊዮን ብር በመመደብ የ2 ነጥብ 6 ኪሎ ሜትር የኮሪደር ልማት ሥራ እያከናወነ ነው፡፡ ይህንን የኮሪደር ልማት ሥራም ከአንድ ወር በኋላ ተጠናቅቆ ለአገልግሎት ክፍት ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል፡፡

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፤ ከተማ አስተዳደሩ ሰባት ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የኮሪደር ልማት ሥራ ለማከናወን ዕቅድ ይዟል፡፡ ከዚህ ውስጥ በ200 ሚሊዮን ብር 2 ነጥብ 6 ኪሎ ሜትር እየተሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህ ውስጥ ቀሪውን 4 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር ስራ በ500 ሚሊዮን ብር ወጪ በቅርብ ጊዜ እንደሚጀመር ጠቁመዋል፡፡

ከአዲስ አበባና ከሌሎች ትላልቅ ከተሞች ልምድ በመውሰድ ሰፋፊ የከተማ ውበት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ የኮሪደር ልማት ሥራው አሁን ላይ የቴራዞ ንጣፍ ላይ ደርሷል ብለዋል፡፡

የኮሪደር ሥራው የውሃ፣ የቴሌ ኬብል፣ የመብራት ዝርጋታ፣ የትራፊክ መብራትና የደህንነት ካሜራ ገጠማ፣ የጌጠኛ ድንጋይ ንጣፍ፣ የመንገድ ዳር አረንጓዴ ልማት፣ የጎርፍ መቀልበሻና ሌሎች የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ያካተተ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የኮሪደር ልማቱ በከተማው የሚገኙ የመንገድ ዳርቻዎችን የማስዋብና ለእግረኞች ምቹ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው ያሉት አቶ ዳዊት፤ ከኮሪደር

በሆሳዕና ከተማ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ሄዲ አብርሀ

# ጎቤና ሺኖዬ- የመስከረም ሌላኛው ጌጥ


**ማርቆስ በላይ**

የመስከረም ወር ለኢትዮጵያውያን ባለብዙ መልክ ነው፡፡ የክረምቱ ጭለማ አልፎ ብሩህ ወቅት የሚታይበት፤ አበቦች የሚፈኩበት እና ብሩህ ተስፋ የሚለመልምበት፤ በርካታ ብሔረሰቦች አዲስ ዓመታቸውን የሚያከብሩበት ወር ነው፡፡ ለአብነትም ኢሬቻ፣ ያ ሆዴ፣ ዮዮ ጊፋታ፣ ዮ ማስቃላ፣ ማሽቃሮ ከብዙ በጥቂቱ ይገኙበታል፡፡

ጎቤና ሺኖዬም ዓመታዊ የኦሮሞ ወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች የዘመን መለወጫ የብሥራት የአደባባይ ጨዋታ (ካርኒቫል) ነው። ይህ የወጣቶችን ባሕላዊ ክዋኔ የሕዝቦችን አንድነትና ፍቅር የሚያጠናክር የዘመን መለወጫ ባሕላዊ ጨዋታ (ካርኒቫል) መሆኑም ተገልጿል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ

ጎቤና ሺኖዬ-... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





## መብትና ግዴታ - የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች

**ማሕሌት ብዙነህ**

እያንዳንዱ ሰው የዘር፣ የቀለም፣ የፆታ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት ፣የፖለቲካ ወይም አስተሳሰብ ልዩነቶች ሳይለይ ለሁሉም የተሰጠው እኩል መብት እና ግዴታ አለው፡፡

በመሆኑም ያለአንዳች ልዩነት በነፃነትና በሠላም የመኖር፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ እንዲሁም የትምህርት፣ የሕክምና እና የመሳሰሉት አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳለው ሁሉ የሕግ የበላይነትን ወይም ሕገመንግሥቱን

መብትና ግዴታ-... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ለትውልድ የሚተባበሩ ክንዶች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ሐተታ**

ነገ ዛሬ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሆኑም ነገን የተሻለ ለማድረግ ዛሬ መሥራት የግድ ነው፡፡ ዛሬ ደግሞ የሁሉም ናት፤ በተለይ የወጣቱ፡፡

ወጣቱ ትውልድ ዛሬ ላይ ሀገሩን ለመለወጥ የሚያስችል በቂ አቅም አለው፡፡ በከንቱ የባከነ የወጣትነት ዘመን ለነገ ከቁጭት የዘለለ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ለዚህ ደግሞ ለትውልድ ግንባታ ትኩረት መስጠትና በኃላፊነት ስሜት መሥራት ተገቢ መሆኑን ለኢፕድ አስተያየታቸውን የሰጡ ምሑራን ይናገራሉ፡፡

የጋብቻና የቤተሰብ አማካሪ ፓስተር ቸርነት በላይ (ፓስተር ቸሬ) ሀገር ተረካቢ ብቁና ንቁ ዜጋ ለመፍጠር በመጀመሪያ ቤተሰብን መገንባት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

የሰው ልጅ መሠረቱ ቤተሰብ በመሆኑ ወላጆችም ለልጆቻቸው መንገድ ማሳየትና መምራት ይኖርባቸዋል የሚሉት ፓስተር ቸሬ፤ ወጣቱ ትውልድ ለሀገሩ ቀናዒነት አስተሳሰብ እንዲኖረው ማድረግ ከተፈለገ መጀመሪያ ሕጻናት ላይ መሥራት የግድ ይላል ባይ ናቸው፡፡

ሳይታረስ የሚያበቅል መሬት ሳይዘራም የሚያጭድ ገበሬ ባለመኖሩ ልጅነት አምክኖ ወጣትነት ላይ ፍሬ



ፓስተር ቸርነት በላይ

መጠበቅ ሞኝነት እንደሆነ ይመክራሉ፡፡

ቤተ እምነቶች፣ የትምህርት ተቋማት፣ የመገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የተዛባውን ነገር የሚያርቁ የተለያዩ ምሑራን በጋራ በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች ትምህርት መስጠት ሲችሉ ለሀገሩ ቀናዒ ትውልድ መፍጠር



ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን

እንደሚቻል ያመላክታሉ፡፡

አለበለዚያ ወጣቱ ትውልድ እየተባለ የሚሠራው ነገርም ትክክለኛ አስተሳሰብ አይደለም፤ ትክክለኛ ሀገር ተረካቢና ብቁ ዜጋ ለማፍራትም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ

ለትውልድ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ከሻይ ቅጠል ምርት ከሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**ታደሠ ብናልፈው**



<u>አዲስ አበባ</u>፡- በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከአንድ ሺህ 142 ቶን በላይ የሻይ ቅጠል ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ዶላር ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳሬክተር ሣሕለማሪያም ገብረመድኅን ፤ በ2016 በጀት ዓመት ከአንድ ሺህ 142 ቶን በላይ የሻይ ቅጠል ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል ብለዋል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት ከአንድ ሺህ 142 ቶን በላይ የሻይ ቅጠል ምርት ለውጪ ገበያ በማቅረብ ሁለት ነጥብ 30 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል ብለዋል፡፡

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ለውጭ ገበያ ከተላከ የሻይ ቅጠል ምርት ሁለት ነጥብ 30 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፤ ከ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ሲነጻጸር ከ292 ቶን በላይ ብልጫ አለው ያሉት ዳሬክተሩ፤ በገቢም ሲነፃፀር 0 ነጥብ 33 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እድገት አሳይቷል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ የተላከው የሻይ ቅጠል ምርት ለውጭ ገበያ የተላከው ከ2015 ዓ.ም ጋር ሲነፃፀር የ50 ሺህ ቶን ብልጫ ቢኖረውም ሀገሪቱ ካላት አቅም አንጻር ብዙ መሥራት የሚጠይቅ መሆኑን ተናግረዋል።

በቀደሙ ዓመታት በሀገሪቱ ተጠቃሽ የሆኑት የውሸውሸና ጉመሮ የሻይ ቅጠል ምርት በአምስት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ብቻ ያረፈ ነበር፤ የሚገኘውም የውጭ ምንዛሪ በዓመት ከሦስት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚበልጥ አልነበረም፤ ከሻይ ቅጠል ምርት የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ባለውም ሥራ በ2016 ዓ.ም 460 ሚሊዮን ችግኝ በማብዛት 30 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የማልማት ሥራ ተሠርቷል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በሻይ ቅጠል ልማት ላይ ባለሀብቶች በስፋት እየተሳተፉ አይደለም፤ ይህም ሀገሪቱም ማግኘት ያለባትን የውጪ ምንዛሪ እንዳታገኝ እንቅፋት ሆኖባታል ያሉት አቶ ሣሕለማሪያም፤ በዘርፉ ባለሀብቶች በስፋት ተሳትፈው ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ምንዛሪ እንድታገኝ መንግሥት በዘርፉ ለሚሳተፉ ባለሃብቶች የተለያዩ ማበረታቻዎች እያደረገ ነው ብለዋል፡፡

የሻይ ቅጠል ምርት አሲዳማና ተዳፋት በሆኑ መሬቶች ላይ መብቀል የሚችልና ምርት የሚሰጥ በመሆኑ ምርታማነቱን ለማስፋት እየተሠራ ነው፤ የሻይ ቅጠል ምርትን ለማስፋት ከአርሶ አደሮች በተጨማሪ ባለሀብቶች በስፋት ሊሳተፉ ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

የሻይ ቅጠል ምርት አንድ ጊዜ ከተተከለ ለ30 እና 40 ዓመታት ምርቱ የሚቆይና በየ15 ቀኑ ምርቱን በመቅጠፍ ገቢ ማግኘት የሚያስችል ነው ያሉት አቶ ሣሕለማርያም፤ ዘርፉ አትራፊ በመሆኑ ባለሀብቶች በስፋት ሊሳተፉ ይገባል ብለዋል፡፡

የሻይ ቅጠል ምርት ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት ባለፈ ለበርካታ ሥራ አጥ ዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ በሁሉም ክልሎች ለማልማት እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡



ሊዲያ ግርማ



ኮሚሽነር ጌቱ አርጋው



ብፁዕ አቡነ አብርሃም

# የመስቀል ደመራ በዓል ሃይማኖታዊ ትውፊቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከበር የቅድመ ዝግጅት ሥራው ተጠናቋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በአዲስ አበባ የመስቀል ደመራ በዓል ሃይማኖታዊ ትውፊቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከበር አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራ መጠናቀቁን የመዲናዋ የሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዘንድሮውን የመስቀል ደመራ በዓል አከባበር ዝግጅትን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር ውይይት አድርጓል።

የአዲስ አበባ ሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ሊዲያ ግርማ የመስቀል ደመራ በዓል ሃይማኖታዊ ትውፊቱንና ሠላምን በሚገልፅ መልኩ እንዲከበር ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት መደረጉን ገልጸዋል።

የመስቀል ደመራ በዓል በሠላም ተከብሮ እንዲጠናቀቅ አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ መጠናቀቁንም አመልክተዋል።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌቱ አርጋው በበኩላቸው በዓሉ በሠላም ተከብሮ እንዲጠናቀቅ ፖሊስ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቁን ገልጸዋል።

በዓሉ በሠላም እንዲከበር ፖሊስ በአዲስ አበባ ካሉ አድባራት ጋር በቅርበት እንደሚሠራም አመልክተዋል።

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፤ የባሕር ዳር እና ሰሜን ጎጃም አሕጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም በዓሉ ፍጹም ደማቅና ሠላማዊ ሆኖ እንዲከበር የከተማ አስተዳደሩ እያደረገ ላለው ሥራ ምስጋና አቅርበዋል።

የደመራ በዓል በታቀደው መንገድ ሠላምንና አንድነትን በሚገልፅ መልኩ ተከብሮ እንዲጠናቀቅ ምዕመኑ ከፀጥታ አካላት ጋር በትብብር እንዲሠራ ጥሪ ማቅረባቸውን ከከንቲባ ጽሕፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

# ዝናብ በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል

**ዳግማዊት አበበ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በመጪዎቹ 10 ቀናት በአንዳንድ ስፍራዎች የሚዘንበው ዝናብ የደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ሲል የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ፤ በመጪው አስር ቀናት በአብዛኛው በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ ይህም ለግብርናው እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና የሚፈጥር ምቹ የእርጥበት ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

ሆኖም በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ ሊኖር ስለሚችል የሚጠበቀው እርጥበት በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስቀድሞ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡

የሚኖረው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ እንዲሁም ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለፍራፍሬ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎትን ለማሟላት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ኢንስቲትዩቱ ጠቅሷል፡፡

የእርጥበት ሁኔታው በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስፋፋ በመሆኑ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ገልጾ፤ በባሮ አኮቦ፣ ዓባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው አዋሽ፣ ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር የውሃ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ተመላክቷል፡፡

በአንጻሩ ግን ባለፉት የክረምት ወራት ከተገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት ጋር ተያይዞ አሁናዊ የውሃ መጠናቸው በጣም በጨመረባቸው እንደ ተንዳሆ፣ ከሰም፣ ቆቃ፣ ርብ፣ ጣና በለስ እና ፊንጫ ግድቦች በሚገኙባቸው የታችኛው የተፋሰስ ክፍሎች ላይ ከመጠን በላይ የግድብ መሙላት እንዳያስከትል የቅርብ ክትትል ማድረግ እንደሚያስፈልግም ኢንስቲትዩቱ አስጠንቅቋል፡፡

በሌላ በኩል መስከረም የክረምት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን እርጥበት በመጪው የበጋ ደረቅ ወራት ጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችል አግባብ መሰብሰብና ማከማቸት ያስፈልጋል ሲል መግለጫው አመልክቷል፡፡

ዜና

# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የቢራ ገብስን በዘመናዊ ገበያ ለማገበያየት እየሠራ ነው

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



አቶ ባየልኝ ዘርዓይ

አዲስ አበባ፡- በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባውን የቢራ ገብስ ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የቢራ ገብስን በዘመናዊ ግብይት ሥርዓቱ ለማገበያየት እየሠራ መሆኑን አስታወቀ፤ በተጨማሪም ተቋሙ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ባቄላ፣ ኑግና ሽምብራን እንደሚያገበያይ አስታውቋል።

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የስትራቴጂ መምሪያ ኃላፊ የሆኑት አቶ ባየልኝ ዘርዓይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ መንግሥት ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ሲገቡ የነበሩትን የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ ግብዓት ለመተካት ግልጽ የፖሊሲ አቅጣጫ አስቀምጦ እየሠራ ነው። ለዚህም በዓመት እስከ 283 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ ሊያስወጣ የሚችልን የቢራ ገብስ በሀገር ውስጥ አምርቶ በመተካት የውጭ ምንዛሪ ማደጉ አንዱ ማሳያ ነው።

የነፍስ ወከፍ የቢራ እና ተዛማጅ ምርቶች ፍላጎት ማደጉን ተከትሎ የቢራ እና የብቅል ፋብሪካዎች በፍጥነት እየተስፋፉ በመሆኑ ከቢራ ገብስ ፍላጎት ዕድገት ጋር አብሮ የሚሄድ የግብይት አማራጭ እንደሚያስፈልግ በጥናት መለየቱን የገለጹት ኃላፊው፤ አሁን እየተሠራበት ካለው የቢራ ገብስ የውል እና ኢንቨስትመንት እርሻ ትስስር በተጨማሪ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የቢራ ገብስን በዘመናዊ ግብይት በማገበያየት በቢራ ገብስ የእሴት ሠንሠለት እየተስተዋሉ ካሉ ተግዳሮቶች መካከል በግብይት ረገድ ያለውን ማነቆ ለማቃለል እየሠራ እንደሆነ አስረድተዋል።

አቶ ባየልኝ እንደሚሉት፤ የቢራ ገብስ ወደ ዘመናዊ ግብይት ሲገባ የምርቱ ዋጋ በፍላጎት እና አቅርቦት እንዲወሰን፤ ግብይቱ የምርት ጥራትን መሠረት አድርጎ እንዲከናወን፤ የቢራ ገብስ አምራች አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። በተጨማሪም አርሶደሮች ለምርት ጥራት እና ምርታማነት ትኩረት እንዲሰጡ ያግዛል። በተመሳሳይ የብቅል እና ቢራ ፋብሪካዎች አስተማማኝ የግብዓት አቅርቦት እንዲኖራቸውም የመፍትሔ አቅም ይሆናል።

የቢራ ገብስ የግብይት ኮንትራትን በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በአማራጭነት ለማገበያየት የግብይት ኮንትራት በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መፅደቁን በመግለጽ፤ በቅርቡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የቢራ ገብስን ማገበያየት እንደሚጀምር ጠቁመዋል።

ከ25 ሺህ በላይ ደንበኞች ያሉት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በ2017 ዓ.ም ከቢራ ገብስ በተጨማሪ ለውጭ ገበያ የሚያቀርባቸው ሰብሎች እንዳሉ የጠቆሙት አቶ ባየልኝ፤ ባቄላ፣ ሽምብራ እና ኑግ ምርቶችን የሚያገበያይ መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለፉት 16 ዓመታት ቡናን ጨምሮ ከ24 የሚበልጡ የጥራጥሬ፣ የቅባት እና የቅመማቅመም ሰብሎች ግብይት እየተፈጸመባቸው እንደሆነ የሚያነሱት ኃላፊው፤ ከነዚህ ውስጥም በዓመት ከ30 ሚሊዮን በላይ የጥራጥሬ እና ከስምንት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የቅባት ሰብሎችን የምታመርተው ሀገር ወደ ውጭ የትልከው የጥራጥሬ እና የቅባት ሰብሎች ድርሻ ከ25 በመቶ እንደማይበልጥ አመላክተዋል።

ባቄላ፣ ሽምብራ እና ኑግ ወደ ዘመናዊ ግብይት እንዲገቡ የማድረጉ ሥራም ይህንን ችግር መፍታትና የምርት አቅርቦት ፍሰቱን ከማሻሻል ጋር የተያያዘ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ከዘርፉ የምታገኘውን የውጭ ምንዛሪ በዚህ መልኩ ማሳደግ እንደምትችልም አብራርተዋል።

# ኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ 391 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዷል

**አዲሱ ገረመው**



አቶ ደበሌ ቃበታ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን በ2017 በጀት ዓመት ከወጪ ንግድ ሥርዓቱ ከፍተኛ የተባለለትን 391 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ማቀዱን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን በመንግሥት የተሰጠውን ኃላፊነት በመወጣት በ2016 ዓ.ም በተቋም ግንባታ፣ እንዲሁም የሀገሪቷ የንግድ ሥርዓት የሚያመነጨውን ገቢ በመሰብሰብ፤ የኢንቨስትመንት አገልግሎቶችን በሙሉ በማሳለጥና በመደገፍ፤ የወጪ ገቢ የንግድ ሥርዓቱን የሚያውኩ የኮንትሮባንድ ንግድና መሰል ወንጀሎችን በመቆጣጠር ረገድ መጠነ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል። በ2017 ዓ.ም በተመሳሳይ የላቀ ሥራ ለመሥራት ታቅዶ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን፤ 391 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብም ታስቧል።

የወጪ ንግድ ሥርዓቱን፤ የኤክስፖርት ሥርዓቱንና፤ የሀገሪቱን የማኑፋክቸሪንግና የግብርና ሥርዓቱን በማገዝ አጠቃላይ የሀገሪቷን የኢኮኖሚ ግስጋሴ ለመደገፍ፤ እንዲሁም የንግድና የሎጀስቲክ ሥርዓትን ለመደገፍ ከፍተኛ እቅድና ግብ በማስቀመጥ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩን ኮሚሽነሩ አስታውቀዋል። በተለይም ከገቢ አሰባሰብ አኳያ ከወጪ ንግድ ሥርዓቱ ከፍተኛ የተባለለትን 391 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ግብ ተጥሎ ወደ ሥራ እንደተገባ ገልጸዋል።

አጠቃላይ የንግዱን፣ የገቢውና የኤክስፖርት ሥርዓቱን፣ የሎጀስቲክስ ሥርዓቱንና የገቢውን ሥርዓት ከሚያውኩ ወንጀሎች መካከል የገቢና ወጪ ኮንትሮባንድ እንዲሁም የሕገ ወጥ ንግድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠርም በትኩረት እንደሚሠራ ተናግረዋል።

ኮሚሽነሩ፤ ገቢ ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው በመጥቀስ፤ ኮሚሽኑ ባለፉት ዓመታትም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን ጠቁመዋል። በተያዘው ዓመትም እቅዱን ለማሳካት የጀመራቸውን ተግባራት አጠናክሮ እንደሚቀጥልና ከሌላው ጊዜ በተሻለ መልኩ እቅዱን ለመፈጸም የሚያስችለውን እንቅስቃሴ መጀመሩን አመላክተዋል።

እቅዶቹ በውጤት ከግብ ሊደርሱ የሚችሉት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተሠማራበት ዘርፍ ሁሉ ለገቢው ስኬት አብሮ በመሥራትና ድጋፍ በማድረግ የራሱን ድርሻ መወጣት እንዳለበትም ኮሚሽኑ አሳስበዋል።

ውጤቱ በተናጠል የሚመጣ አይደለም ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በበጀት ዓመቱ የታቀዱ ሁለንተናዊ ተግባራትን በከፍተኛ ውጤት ለማጠቃለል የሕዝቡ ያላሰለሰ ጥረት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል። ለአብሮነት ሥራው ሁሉም እንዲረባረብ ጥሪ አቅርበዋል።



አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ

## የተመድ የፀጥታው ምክር ቤት ማሻሻያ የአፍሪካን እውነተኛ ውክልና ባረጋገጥ መልኩ እንዲከናወን ተጠየቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኒውዮርክ እየተካሄደ ባለው 79ኛው የ.ተ.መ.ድ. ጠቅላላ ጉባዔ የዋና ፀሐፊው አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ኢኒሼቲቭ የሆነውና ከ140 በላይ የሀገር መሪዎች የሚሳተፉበት የመጪው ጊዜ ጉባዔ (Summit of the Future) ተከፍቷል።

በዚሁ ጉባዔ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ክቡር አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ የተመራ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን እየተሣተፈ ይገኛል።

በጉባዔው ላይ ክቡር ሚኒስትሩ ባሰሙት ንግግር የተመድ የፀጥታው ምክር ቤት ማሻሻያ የአፍሪካን እውነተኛ ውክልና ባረጋገጠ መልኩ እንዲከናወን ጠይቀዋል።

አምባሳደር ታዬ ምክር ቤቱን ለማሻሻል የሚደረገው እንቅስቃሴ የአፍሪካን የውክልና አድማስ ከሁሉም መመዘኛዎች አንጻር ታሳቢ ሊያደርግ እንደሚገባው ጠይቀዋል።

ስምምነቱ ሁሉንም ሀገራት በእኩል አይን የሚመለከተው ጊዜ አይሽሬ የሆነው የተመድ መመሥረቻ ቻርተር ሳይሸራረፍ እንዲተገበር ለማድረግ የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል።

በመጪው ጊዜ ጉባዔ ላይ የባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ ሥርዓትን ሪፎርም ለማድረግ በትውልድ የአንድ ጊዜ ዕድል ይሆናል ተብሎ የሚጠበቅ ጉባዔ ሠነድ ከ143 ሀገራት በላይ ድጋፍ በማግኘት ፀድቋል።

አምባሳደር ታዬ ስምምነቱ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት በሚደረገው ጥረት የሚታዩ ክፍተቶችን ለማስተካከል ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው አንስተዋል።

ሚኒስትሩ ሀገራት ድህነትን ለማጥፋት የሚያደርጉት ጥረት በራሳቸው የፖሊሲ ማዕቀፍ ምርጫ አግባብ የተጠናከረ ድጋፍ እንዲደረግላቸው እና ለጉዳዩ ቀዳሚ ትኩረት እና የፖለቲካ ቁርጠኝነት እንዲኖር ጠይቀዋል።

ኢትዮጵያ በጉባዔው የፀደቁት ሠነዶች Pact for the Future, Declaration on Future Generations, Global Digital Compact የድርድር ሂደት ላይ ተሳትፎ ስታደርግ ቆይታለች።

የሠነዱ መፅደቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ድህነት፣ ረሃብ፣ የአየር ንብረት ቀውስ፣ አደገኛ ግጭቶች፣ ወረርሽኞች እና ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር ተያይዘው የሚመጡ አደጋዎች እያደጉ በሚገኙበት ወቅት፣ የጋራ ምላሽ እና መፍትሔ ለመስጠት ዕድል እንደሚፈጥር ታምኖበታል።

# ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ ለመሆን የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት እያደረገ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ሀዋሳ፡-ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በቀጣይ ዓመት ራስ ገዝ ለመሆን የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ገለጹ።

የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ፍስሐ ጌታቸው (ዶ/ር) ለኢዜአ እንደገለጹት፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የምርምርና የልህቀት ማዕከል እንዲሆኑና ራሳቸውን እንዲችሉ ከተለዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ አንዱ ነው።

በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ ራስ ገዝ ሲሆን የሚሠራባቸው አምስት ዘርፎች ተለይተው የቅድመ ዝግጅት ሥራ መጀመሩን ተናግረዋል።

“ግብርናና ላይፍ ሳይንስ፣ የጤና ሳይንስና ሕክምና፣ ፊዚካል ሳይንስ፣ ማኅበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ እንዲሁም የመምህራን ሥልጠና የተለዩ አምስቱ ዘርፎች ናቸው” ሲሉም ገልጸዋል።

በእነዚህ አምስት ዘርፎች ብቁና ተመራማሪ ዜጋ ለማፍራት የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውንም አስታውቀዋል።

በእነዚህ ዘርፎች የሥርዓተ ትምህርት ክለሳ፣ የበዙ መርሐ ግብሮችንም ወደ አንድ የማምጣትና ሥርዓተ ትምህርት የማዘጋጀት ሥራ እንደሚሠራም ተናግረዋል።

ከዘርፎች ልየታ ጎን ለጎን ትምህርቶችን በዲጂታል ታግዞ ለመስጠት፣ በቤተ መጽሐፍት የሚኖሩ የኤሌክትሮኒክስ መጽሐፍት ክምችትን ለማሳደግ እና ተማሪዎችም መጽሐፍቱን ባሉበት ቦታ ሆነው መጠቀም የሚያስችላቸው መሠረተ ልማት መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

መምህራን ትምህርቶችን በቪዲዮ ምስል አስደግፈው መስጠት የሚችሉበት ክህሎት እንዲኖራቸው ለማድረግ ከአሪዞና ስቴት ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለ400 መምህራን የኦን ላይን ሥልጠና መሰጠቱንም ምክትል ፕሬዚዳንቱ አመልክተዋል።

ለዚህም በዩኒቨርሲቲው የተሟላ መሣሪያ ያለው የመልቲ ሚዲያ ስቱዲዮ በማቋቋም ሙሉ ዝግጅት መደረጉንም ነው የገለጹት።

በተያዘው ትምህርት ዘመን ዩኒቨርሲቲው በመጀመሪያ፣ በሁለተኛና በሦስተኛ ዲግሪ የትምህርት ፕሮግራሞች ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅቱን ማጠናቀቁንም ምክትል ፕሬዚዳንቱ አያይዘው ገልጸዋል።

በትምህርት ዘመኑ በ267 የትምህርት መስኮች ተማሪዎችን ለመቀበል መዘጋጀቱንና ከእነዚህ የትምህርት መስኮች 35 በመቶ የሚሆኑት በቅድመ ምረቃ የሚሰጡ የትምህርት መስኮች መሆናቸውን አስረድተዋል።

ኢንጂነር ፍስሐ (ዶ/ር) እንደገለጹት በዩኒቨርሲቲው በፀደቀው የትምህርት ካላንደር መሠረት የመማር ማስተማር ሥራው በመጪው መስከረም 22 ቀን 2017 ዓ.ም ይጀመራል።

ዩኒቨርሲቲው ለትምህርት ጥራት በሰጠው ትኩረት ውጤት የታየ መሆኑን የተናገሩት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ ለእዚህም አምና ካስመረቃቸው ተማሪዎች 90 በመቶ የመውጫ ፈተናው ማለፋቸውን በማሳያነት ጠቅሰዋል።

# መብትና ግዴታ -...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የማክበር፣ ግብር በአግባቡ የመክፈል እና ያሉ ልዩነቶችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

መብት እና ግዴታ የማይነጣጠሉ ነገሮች ሲሆኑ ግዴታውን ሳይወጣ ለመብት መከራከር ተገቢ አይደለም፡፡ ታዲያ ሰዎች መብትና ግዴታቸውን ምን ያህል ይገነዘባሉ፤ ምን ያህሉንስ ይጠቀሙበታል ሲል ኢፕድ የሕግ ባለሙያዎችን አነጋግሯል፡፡

በተፈጥሮ የሚገኝ መሠረታዊ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች እና በሕግ እውቅና የሚሰጣቸው መብት እና ግዴታዎች አሉ ያሉት የሕግ ባለሙያው አቶ ደበበ ኃይለገብርኤል ናቸው፡፡

አቶ ደበበ እንደገለጹት፤ አንድ ሦስተኛ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ስለሰብዓዊ መብት ይናገራል፤ እውቅና ይሰጣል፡፡ ይህም ዜጎች ሀሳባቸውን በነፃነት የመግለጽ፣ የፈለጉትን እምነት የመከተል፣ የመሰብሰብና ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት እንዳላቸው በሕግጋት እውቅና እና ጥበቃ ይደረግላቸዋል ፡፡

እነዚህ ለእያንዳንዱ ዜጋ በእኩልነት የተሰጡ መብቶችም በባሕሪያቸው ልቅ አይሆኑም ያሉት አቶ ደበበ፤ የሌላውን መብት ለመጠበቅ ሲባል በመብቶች ላይ የሚጣሉ ገደቦች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡

ለምሳሌም ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ምንም እንኳን መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት ቢሆንም መብቱ ሊከበርና ሊጠበቅ የሚችለው በሌላው ላይ ጉዳት እስካላደረሰ ብቻ ሲሆን መሆኑን አንስተው፤ ስለዚህም ሰዎች የሌሎችን መብት የማክበር ግዴታ ይኖርባቸዋል ይላሉ፡፡

በመሆኑም ዜጎች ላይ በዋነኝነት የሚወድቀው ግዴታ የሚሆነው የራሳቸውን መብት በሚጠቀሙበት ወቅት በተመሳሳይ የሌላውን መብት የማክበር ግዴታ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ከዜጎች በተጨማሪም መንግሥት ሦስት ዋና ዋና ግዴታዎች አሉበት፡፡ ከእነዚህም ሕግ በማውጣትና ተቋማትን በመመሥረት መብትን የመጠበቅ ግዴታ እና ለወጡት መብትና ግዴታዎች እውቅና የመስጠት ኃላፊነት እንዳለበት ይጠቅሳሉ፡፡

እንዲሁም በባሕሪያቸው መንግሥት እንዲያሟላቸው የሚጠበቁ ለዜጎች እንደመኖሪያ ቤት እና የመሠረተ ልማት ማሟላት መብቶችን አቅሙ በፈቀደ መጠን እንዲያሟላ መንግሥት ይጠበቅበታል፡፡

በኢትዮጵያ እስካሁን ከ1400 በላይ አዋጆች ያሉ ሲሆን ዜጎችም ሆነ ስለአዋጁ የሚመለከታቸው አካላት በአዋጁ ላይ ስለሰፈረው መብት እና ግዴታ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆኑን አቶ ደበበ ይናገራሉ፡፡

እንዲሁም የተሰጣቸው መብት ገደቡ የት ድረስ እንደሆነ እና የሚጠበቅባቸው ግዴታ መኖሩን እንኳን ካለመገንዘብ ሰዎች በየአካባቢው ለተለያዩ ግጭቶችና ችግሮች ሲዳረጉ ይስተዋላል፡፡

ሕግን አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም ያሉት አቶ ደበበ፤ ለዚህም መንግሥት ላይ ከወደቁ ግዴታዎች ውስጥ አንዱ የሆነው ዜጎች መብት እና ግዴታቸውን እንዲያውቁ የማድረግ ግዴታና ኃላፊነት መወጣት አለበት ብለዋል፡፡

በመሆኑም መንግሥት የሚያወጣቸውን ሕጎች ሕዝብ እንዲያቅ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም በቂ ስላልሆነ በተለያዩ ቋንቋዎችና አካባቢዎች ተደራሽ ማድረግ እንዳለበት ጠቅሰዋል ፡፡

እንዲሁም መንግሥትን በማገዝ የሚሠሩ እንደ የሲቪል ማኅበራት፣ ሕግ ባለሙያዎች እና ሚዲያ አካላት ዜጎች መብታቸውን እንዲያውቁ የማስተማርና ግንዛቤ የመፍጠር ኃላፊነት አለባቸው ብለዋል፡፡

ዜጎችም ስለተሰጣቸው መብትና ስለሚጠበቅባቸው ግዴታ በማንበብ እና ከሚመለከታቸው የሕግ አካላትን በመጠየቅ በቂ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ሌላው የሕግ ባለሙያ አቶ ገመቺስ መኮንን በበኩላቸው፤ መብትና ግዴታ ሕግን መሠረት ባደረገ ሕገመንግሥትና ከሕገመንግስቱ በታች ተፈጻሚነት ያላቸው እንደአዋጅ፣ መመሪያና ደንብ የመሳሰሉት የራሳቸው የሕግ አወጣጥ ሥርዓት ባላቸው አካላት  የሚቀመጡ ሰነዶች ናቸው ይላሉ፡፡

ሰነዶቹ የተወሰኑ ሰዎች ሀሳብ ብቻ ሳይሆን የማኅበረሰቡ እሴትና ሀሳብ ነፀብራቅ ሲሆኑ ሥልጣን ባለው አካል እንደመብትም እንደግዴታም የተቀመጡ ነገሮች ናቸው፡፡

ለሰዎች ከተሰጡት ከሕግ የሚመነጭ ሕገመንግሥታዊና ከሰብዓዊ መብትና ግዴታዎች በተጨማሪም በግለሰቦች፣ በተቋምና በማኅበራት ስምምነትና ከውል ሊመነጩ እንደሚችልም ይገልጻሉ፡፡

አቶ ገመቺስ እንደገለጹትም፤ እያንዳንዱ ሰው በመብቶቹና በግዴታዎቹ አፈጻጸም ዙሪያ የማወቅ እኩል መብት አለው፡፡ መብቱ የተነካበት ሰው የውስጥ አሠራርና ደንቦች ከመጠቀም ጀምሮ የግልግል ሂደቶችን በመከተል መብቱን ሊያስጠብቅ ይችላል፡፡

በፍርድ ቤት ውስጥም የፍታሐ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግ እና በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ በተደነገገ አካሄድ ላይ መብትና ግዴታን ማስጠበቅ የሚቻል መሆኑን አንስተው፤ ሁሉም ሰው ሕጉ ደህንነቱ እንዲጠበቅለት እኩል የሆነ መብት አለው፡፡

“አብዛኛው ማኅበረሰብ መብትና ግዴታን በተመለከተ ብዙም ግንዛቤ የለውም፤ በመተግበር ላይ ክፍተት አለ” ያሉት አቶ ገመቺስ፤ በመጀመሪያ ግዴታችንን ስንወጣ መብታችን መጠየቅ እንችላለን  ይላሉ፡፡

በመሆኑም ሰዎች መብትና ግዴታዎችን በማንበብ፣ የሕግ ባለሙያዎችን በማማከር ማወቅ፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትም ውስጣዊ ሕጎችን ለሚመለከታቸው ሁሉ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡

# ስትውልድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ልጅነት ላይ መሥራት አስፈላጊ ነው፡፡

“ልጅነት ላይ ያልተዘራ ዘር በወጣትነት ወቅት ሊገኝ አይችልም፤ ወጣትነት ላይ ያልተዘራም ሽምግልና ላይ ሊገኝ አይችልም”፤ የሚሉት ፓስተሩ፤ ልጆችን መሥራት ማለት ዛሬና ነገን በድምሩ እንደመሥራት እንደሆነ ያክላሉ፡፡

“ከዚህ በፊት የነበሩ የሃይማኖት አባቶች በሚገባ ሠርተዋል፤ ነገር ግን አሁን ላይ የቤተ እምነቶች ቁጥር ከማብዛት ውጪ በትውልድ ላይ ብዙም እየተሠራ አይደለም” የሚሉት ፓስተር ቸሬ፤ የርስ በርስ ግድያ፣ መፈናቀል፣ ከባሕል ከእምነት፣ ከወግና ልማድ፣ ያፈነገጡ እኩይ ድርጊቶች መበራከት ጥላቻና ጸያፍ ቃላት ለዚህ ማሳያዎች ናቸው ይላሉ፡፡

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን በበኩላቸው ብቁና ንቁ እንዲሁም ለሀገሩ ቀናዒ የሆነ ዜጋ ለመፍጠር ብሎም ነገን የተሻለ ለማድረግ በተለይ ትምህርት ቤቶች ላይ ሰፋፊ ሥራዎች መሥራት አስፈላጊ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ማለት ትምህርት ቤት ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉ ዜጋ ቀዳሚ ኃላፊነት መሆኑ ሊታሰብበት እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

ከአኗኗር ለውጥ ጋር ተያይዞ በቤተሰብ፣ በአካባቢ እንዲሁም በሀገር ሽማግሌዎች ለአዲሱ ትውልድ የሚሰጥ የነበረው ምክር ቀንሷል የሚሉት ልጅ ዳንኤል፤ ይህንን የተካው ትምህርት ቤት በመሆኑ ትምህርት ቤት ላይ ትኩረት ያደረገ ሥራ መሥራት አለበት፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም አሁን ላይ ዓለም በቴክኖሎጂው በፍጥነት እየተቀየረች ያለችበት ሰዓት ስለሆነ በቴክኖሎጂው ዘርፉ እንዲበቁ ማድረግና በተለይ ወደ ፈጠራውና ኢኖቬሽን ዘርፍ ላይ በሰፊው እንዲሳተፉ መድረግም ተገቢ እንደሆነ ያነሳሉ፡፡

እንደ ልጅ ዳንኤል ገለጻ፤ ኅብረተሰቡም የቀድሞ መልካም ልማዱን በማነቃነቅ አዲሱን ትውልድ መገሰጽና መምከር አለበት፡፡ በተጨማሪም በየዘርፉ የሚገኙ ባለድርሻ አካላትም የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት አለባቸው፡፡

የአርበኞችን የድል ታሪክና የአባቶችን ተጋድሎ እንዲሁም ለሀገር ዕድገትና አንድነት የሠሩትን በርካታ ሥራዎች የአሁኑ ትውልድ በሥራ፣ በትምህርት፣ የሀገርን አንድነትን እና ሉዓላዊነትን በማስጠበቅ እንዲሁም በተለያዩ የሙያ ዘርፎች መድገም እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡

ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ደረጃ እንድትደርስ ጀግኖች አርበኞች ደማቸውን አፍስሰውና አጥንታቸውን ከስክሰው የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለውባታል፤ ይህን ትውልድ በተገቢው መንገድ መገንዘብ እንዲችል መሥራት እንዳለበትም ምክረ ሃሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡

# ጎቤና ሺኖዬ- ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጀሚላ ሲምቢሩ ትላንት በተጠናቀቀው ስድስተኛ ዙር "ጎቤና ሺኖዬ" የወጣቶች የባሕላዊ ጭፈራ ፌስቲቫል ላይ ተገኝተው እንደገለጹት፣ "ጎቤና ሺኖዬ" ወጣት ወንዶችና ሴቶች ክረምቱ አልፎ የብራ ወቅት መምጣቱን ለማመላከት በባሕላዊ አልባሳት አጊጠው የሚጨፍሩት ባሕላዊ ጭፈራ ነው ይላሉ።

የ"ጎቤና ሺኖዬ" አዲስ ዓመትን የባሕላዊ ጭፈራ ፌስቲቫል ከጳጉሜ 1 ቀን 2016 ጀምሮ ሲከናወን መቆየቱን ጠቅሰው፣ በፌስቲቫሉ ወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች የተለያዩ ባሕላዊ አልባሳት አጊጠው ትውፊቱን በጠበቀ መልኩ ሲያከብሩ መቆየታቸውን ይገልጻሉ።

ወጣቶቹ በተለያዩ ጎዳናዎች፣ በታዋቂ ግለሰቦችና በመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች መኖሪያ ቤት የእንኳን አደረሳችሁ መልካም ምኞት ሲገልጹና የተለያዩ ስጦታዎችን ሲቀበሉ መቆየታቸውንም የገለጹት ኃላፊዋ፣ ፌስቲቫሉ ወጣቶች አንድነታቸውን ያጠናከሩበት፣ ደስታቸውን ያጋሩበትና ተስፋቸውን ያንጸባረቁበት እንደነበርም ይናገራሉ።

የኦሮሞ ሕዝብ በመስከረም ወር መጀመሪያ ከሚያከብራቸው ባሕላዊ ጭፈራዎች መካከል "ጎቤና ሺኖዬ" አንዱ መሆኑን ገልጸው፣ ወጣቶች የአዲሱን ዓመት መምጣት የሚያውጁበትና አንድነታቸውን የሚያሳድጉበት፣ የሚገናኙበት፣ ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩበት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የአደባባይ በዓላት ዜጎች ማንነታቸውን፣ ባሕላቸውንና ቋንቋቸውን እንዲያስተዋውቁ ምቹ ሁኔታዎችን እንደፈጠሩ በመግለጽ፣ መንግሥት ባሕላዊ ማንነቶች በአደባባይ እንዲገለጡ በልዩ ትኩረት እየሠራ እንደሚገኝም ይገልጻሉ፡፡

ከሰሜን ሸዋ የመጣው ወጣት ሰይፉ ቱራ ደበሌ እንደተናገረው፣ የ"ጎቤና ሺኖዬ" ወጣቶች ባሕላችንን፣ ቋንቋችንንና ማንነታችንን በአደባባይ ወጥተን የምናሳይበት ነው ሲል ይናገራል፡፡

ቀደም ሲል የ"ጎቤና ሺኖዬ" ጭፈራዎች ወጣቶች በየመንደሩ ሲያከብሩ እንደነበርና አሁን ግን በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ በባሕላዊ አልባሳት ደምቀው በአደባባይ መከበሩ ልዩ ስሜት እንደፈጠረበት ያስረዳል፡፡

ባሕላዊ ጭፈራ ወጣቶችና ልጃገረዶች ተሰባስበው አንድነትን የሚያሳዩበት መሆኑን በመግለጽ፣ አንድነትን መፍጠር ከተቻለ ባሕልን ማስተዋወቅ፣ ሠላምን ማረጋገጥ፣ ልማትን ማምጣት እንደሚቻል ይገልጻል፡፡

የ"ጎቤና ሺኖዬ" በርካታ ወጣቶች የሚሳተፉበት በመሆኑ በዓሉን አጎልብቶ ለሀገር አንድነትና ሠላም ማዋል ተገቢ ነው የሚለው ደግሞ ወጣት ብሩክ ግርማ ነው፡፡

ለሀገር አንድነትና ሠላም ትልቁን ሚና የሚጫወተው ወጣቱ ነው የሚለው ወጣት ብሩክ፣ ወጣቶች የራሳቸውን ባሕልና ማንነት ይዘው በአደባባይ ተገልጠው የሚተዋወቁበት፣ ስለሀገራቸው ዕጣ ፈንታ የሚወስኑበትንና የሚመክሩበትን ዕድል መፍጠር ተገቢ መሆኑን ይናገራል፡፡

በተለያዩ የሀገሪቱ ጫፍና ጫፍ የሚገኙ ወጣቶች የሚገናኙበትን ዓውድ መፍጠር እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፣ በክልል ደረጃ የተጀመረው የ"ጎቤና ሺኖዬ" የአደባባይ በዓል በሀገር አቀፍ ደረጃም መፈጠር እንዳለበት ያስረዳል፡፡

አዲሱን ዓመት የሠላም ፍቅር፣ የብልፅግና የሚሆንበትን መንገድ ወጣቶች ተገናኝተው፣ ተግባብተው፣ ስለ ሠላም አንድነት ሲነጋገሩ ተግባራዊ እንደሚሆን ወጣት ብሩክ ይናገራል፡፡

የአደባባይ በዓላት የግጭት ምንጭ መሆን እንደሌለባቸውና ባሕል ፖለቲካ የሌለበት በመሆኑ ሰዎችን የሚያጋጭ አንድም ነገር እንደሌለ በመግለጽ፣ ማኅበረሰብ ውስጥ የነበረን እሴትና ባሕልን በአደባባይ መግለጥ ለሀገራዊ አንድነትና ሠላም አቅም እንደሚሆን ይገልጻል፡፡



# በሆሳዕና ከተማ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ልማቱ ጋር የተገናኘ ሁለት ዘመናዊ መፀዳጃ ቤቶች ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን ተጨማሪ አምስት መፀዳጃ ቤቶች እየተገነቡ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

የመንገድ ዳርቻ አረንጓዴ ልማት ሥራና ሌሎች ግንባታዎች ለከተማዋ አዲስ ገጽታ የሚያጎናጽፍና ለነዋሪዎቿ ብሎም ለእንግዶቿ ምቹ እንዲሁም ተስማሚ የማረፊያ ሥፍራን ስለሚፈጥር በልዩ ትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ አቶ ዳዊት ተናግረዋል።

በተጨማሪ በ100 ሚሊዮን ብር ወጪ በከተማው 102 ሄክታር መሬት የሚሸፍን ሁለገብ የሕዝብ መዝናኛ ፓርክ ግንባታ የመጀመሪያው ምዕራፍ ሥራ መጀመሩን አመላክተዋል፡፡

እየተገነቡ ያሉ መሠረተ ልማቶች ለከተማው ውበት ከመስጠት ባሻገር ለብዙ ሰዎች ሥራ ዕድል እንደሚፈጥር ገልጸው፤ የተጀመሩ ሥራዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው ለኅብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ከኅብረተሰቡ ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የሚገነቡ መሠረተ ልማቶች ሲጠናቀቁ ማኅበረሰቡ በባለቤትነት ስሜት ሊንከባከበውና ሊጠቀምበት እንደሚገባ አቶ ዳዊት አስረድተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከቱሪዝም አዝመራው ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት በትኩረት መሥራት የሚያስፈልግበት ወቅት!

በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የምጣኔ ሀብቱ ምሰሶ ተብለው ከተያዙት አምስቱ የምጣኔ ሀብቱ ዘርፎች መካከል አንዱ የቱሪዝም ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል። ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ያለበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታል።

ዘርፉ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመሆን፣ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ኢኮኖሚውን በማንቀሳቀስና የሀገር ገጽታን በመገንባት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው እንደመሆኑ ከዘርፉ የሚጠበቁትን ለማግኘት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ይገኛሉ።

አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎችንና መሠረተ ልማቶችን የመገንባት፣ ነባሮቹን ለጎብኚዎች ምቹ የማድረግ፣ መስሕቦችን የማስተዋወቅና ለገበያ የማቅረብ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። የመስሕብ ስፍራዎችን በዩኔስኮ እንዲመዘገቡ ለማድረግ እየተሠራ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎም በርካታ መስሕቦችን በዩኔስኮ ማስመዝገብ ተችሏል።

ለዘርፉ ፋይዳቸው ከፍተኛ ነው ተብለው የታመናባቸው ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብቶች ትኩረት እንዲሰጣቸው፣ እንዲለሙ፣ እንዲተዋወቁና ለገበያ እንዲቀርቡ፣ የቱሪዝም ዘርፉ ተዋንያንንና መላው ሕዝብ የሚገናኙባቸውን ኤግዚቢሽኖች ማካሄድና ትስስሮች እንዲፈጥሩ ማድረግ ላይ ተሠርቷል፤ እየተሠራም ነው።

በተለይ ለዘርፉ ልማት እምቅ አቅም አላቸው በተባሉ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ በዓላት ወቅት የውጭ እና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ጉብኝት እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። ከትራንስፖርት፣ ከፀጥታና ደኅንነት፣ ወዘተ ጋር ተያይዞ ችግሮች እንዳይገጥሙ ከሕዝቡ ጋር አስቀድሞ መሥራት ተለምዷል።

ሀገሪቱ በቱሪዝም ዘርፍ አሟጣ ልትጠቀምባቸው የሚገባ ወቅቶች እንዳሏት ይታወቃል። በእነዚህ ወቅቶች በርካታ የውጭ ቱሪስቶች ወደ ሀገሪቱ እንደሚመጡም ይታወቃል፤ በሀገር ውስጥ ከፍተኛ የጉዞና የመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች የሚደረጉባቸው በዓላትና የመሳሰሉት ሥነሥርዓቶች የሚካሄዱባቸው በርካታ ወቅቶች ያሉ ሲሆን፣ ከእነዚህ ወቅቶች አንዱ ይህ የተያዘው የመስከረም ወር ነው።

ይህ ወር ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ብዙ ትርጉም አለው። ወሩ ኢትዮጵያውያን አዲስ ዓመታቸውን የሚጀምሩበት፣ ከጨለማው የክረምት ወቅት ወደ ብርሃናማው የበጋ ወቅት ሽግግር የሚያደርጉበት፣ ወንዞች የሚጎድሉበት፣ ዝናቡ ከአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢ መሸሽ የሚጀምርበት፣ ነፋሻማ አየር ስፍራውን የሚይዝበት፣ እሸት በስፋት መድረስ የሚጀምርበት፣ ሰውም ከብቱም ሰብሉም ምቹ የአየር ሁኔታ የሚያገኝበት ተወዳጅ ወር ነው።

በዩኔስኮ በማይዳሰስ ቅርስነት የተመዘገበው የመስቀል ደመራ በዓልን የክርስትና እምነት ተከታዮች በድምቀት የሚያከብሩበት፣ በርካታ ብሔሮችና ብሔረሰቦች አዲስ ዓመታቸውን የሚያከብሩበት፣ በኦሮሞ ብሔረሰብ ዘንድ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው የኢሬቻ በዓል የሚከበርበት ወር ነው።

በኢትዮጵያ ለብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት እንዲሁም ለሃይማኖት እኩልነት የተሰጠው ትኩረት እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ ባሕላዊ እሴቶቻቸውንና እምነታቸውን፣ ወዘተ በአደባባይ የሚከብሩበት ሁኔታ ይህን ወር በባሕላዊ ሥነሥርዓቶች ይበልጥ ደማቅ እንዲሆን አድርጎታል።

ወቅቱ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በእጅጉ እንዲሟሟቁ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በዓላቱን በየትውልድ ቀዬያቸው ለማክበር፣ የበዓል አከባበሮችን ለመጎብኘት፣ ክረምት የተራራቀውን ቤተሰብን ለመጠየቅ፣ ወዘተ. ሲሉ ሰዎች በብዛት ሰፊ የጉዞ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። ከትውልድ ሀገራቸው ርቀው የሚገኙትም ወደ ሀገራቸው ከሚመጡባቸው ወቅቶች አንዱ ይሄው ወቅት ነው። በዚህ ሁሉ ውስጥ ደግሞ አያሌ ኢትዮጵያውያን አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ቱሪስት ይሆናሉ። ይህም ለቱሪዝም ዘርፍ ትልቅ አቅም እንደሆነ ይታመናል።

በዚህ ወቅት ደግሞ ለዘርፉ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ በርካታ ክንውኖች የሚካሄዱበት የዓለም ቱሪዝም ቀን በኢትዮጵያ በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል፤ ይህን ቀን ኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፏን ለማንቀሳቀስ ትልቅ አቅም አድርጋ ስትጠቀምበት እንደቆየች ሁሉ ዘንድሮም ይህንኑ ታደርግበታለች።

ይህን ታላቅ የቱሪዝም እንቅስቃሴ የሚደረግበትን ወቅት ኢትዮጵያውያንና መንግሥታቸው በወሳኝ መልኩ ተጠቃሚ ለመሆን በሚገባ ሊሠሩበት ይገባል። ለዚህም የሚመለከታቸው መንግሥታዊና የግል ተቋማት፣ መላው ሕዝብ አበክረው መሥራት ይኖርባቸዋል። ለጎብኚዎች ምቹ ማረፊያዎችን በማመላከት፣ የሚጎበኙ ቦታዎችን በማሳየት፣ የቱሪስት ቁሳቁስን በማቅረብና በመሳሰሉት ሁሉ በስፋት መሥራት ይጠበቃል።

ገቢ ማግኘት አንድ ነገር ሆኖ ጎብኚዎችን በሚገባ ማስተናገድ መቻል በቀጣይም ሀገሪቱ የጎብኚዎች ፍላጎት እንድትሆን የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል። የዘንድሮ ጎብኚዎች ለመጪዎቹ ጎብኚዎች መረጃ ሰጪ እንደመሆናቸው ተገቢውን መረጃ ይዘው እንዲሄዱ ማድረግ ያስፈልጋል፤ እነሱም ተመላልሰው ሀገሪቱን እንዲጎበኙ በጥሩ ሁኔታ ማስተናገድ ይጠበቃል። ጎብኚዎች ዓላማ አድርገው የሚመጡት በዓላቱን ሊሆን ቢችልም፣ ከዚሁ ጎን ለጎን አዳዲሶቹን የቱሪስት መስሕቦችና ነባሮቹን ማስጎብኘት ላይም መሠራት ይኖርበታል።

ይህ ወር አርሶ አደሩ አዝመራ እንደሚሰበስብበት ወቅት ሊታይ ይገባዋል። አዝመራ በወቅቱና በአግባቡ ካልተሰበሰበ ብዙ ከተለፋበት የግብርና ሥራ የሚጠበቀውን ምርት ማግኘት አይቻልም። በቱሪዝም ዘርፉም እንደዚያው ነው። ሀገሪቱ፣ ኅብረተሰቡ፣ ሌሎች የቱሪዝም ዘርፉ ተዋንያን ዘርፉ የሚጠበቅበትን እንዲወጣ ሲሠሩ እንደቆዩ ሁሉ፣ ከእዚህ የቱሪዝም ታላቅ አዝመራ ምርታቸውን ለመሰብሰብ መረባረብ ይኖርባቸዋል።

የቱሪዝም ተዋንያኑ የቱሪስት እንቅስቃሴው እንዲሳለጥ በማድረግ፣ የሠላም ባለቤት የሆነው ሕዝብ ከፀጥታ አካላት ጋር በመሆን ሠላሙን በመጠበቅ የቱሪስቶች ቆይታ የሚራዘምበት፣ ሀገር ተገቢውን ጥቅም የምታገኝበት ሁኔታ እንዲፈጠር አበክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አጀንዳ ተቀባዮች ሳይሆን አጀንዳ ሰጪዎች እንሁን!

**ልዑል ከ6ኪሎ**

የግብፅ ሚዲያዎች ኢትዮጵያን በተመለከተ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የተሳሳተ መረጃ በማሰራጨትና አጀንዳ በመስጠት መጠመድ የጀመሩት ዛሬ አይደለም። ኢትዮጵያ ገና የዓባይን ግድብ የመገንባት እቅዷን ይፋ ካደረገችበት ማግስት ጀምሮ ነው። በዚህም እኩይ ተግባር ከአስርተ ዓመታት በላይ ተሰማርተዋል። ዛሬም የግድቡ ግንባታ ተገባዶ ባለበት ሁኔታ በተመሳሳይ ዘመቻ ላይ ይገኛሉ።

በተለይም ኢትዮጵያና ሶማሊላንድ የወደብ ስምምነት መፈራረማቸውን ተከትሎ እነዚህ መገናኛ ብዙኃን በኢትዮጵያ ላይ የተሳሳተ መረጃ ማሰራጨት የዘወትር ተግባራቸው ሆኗል። የሚገርመው ደግሞ ይህን የሚዲያ ዘመቻ የሚያደርጉት የግብፅ መንግሥትን የሚደግፉ ብቻ ሳይሆኑ የሚቃወሙና በሌላ ሀገር በስደት ላይ የሚገኙ የሀገሪቱ ሚዲያዎች ጭምር ናቸው። የዘገባዎቻቸው ዋነኛ ዓላማም ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ ላይ ጫና እንዲፈጠር ማድረግ ነው።

በግብፅ ሰፊ ስርጭት ያለው አህራም ጋዜጣን ጨምሮ እንደ አሽሩቅ፣ አልጀሙሪያ፣ አል-ሙስጠቅበል አል-ሱልጣን፣ ሰደል-በለድና ሌሎችም በርካታ ጋዜጦች ላይ ኢትዮጵያ ከእለት ተእለት አጀንዳቸው ወርዳ አታውቅም። ጋዜጦቹ በዋናነት “ኢትዮጵያ የሶማሊያን ሉዓላዊነት ጥሳ ሀገሪቱን እንደወረረች” በማስመሰል ኢትዮጵያ ላይ ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲበረታ ለማድረግ እየተጉ ነው።

በዚህም በተለይም የዓረቡ ዓለም ኢትዮጵያን በተመለከተ የተሳሳተ ምልከታ እንዲኖረው የማድረግ ሕልም አላቸው። ለአንዳንድ የምዕራባውያን ሚዲያዎችም እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ ኢትዮጵያን በተመለከተ የተሳሳተ አጀንዳ ለማቀበል ሲጥሩ እለት ተእለት የምናስተውለው እውነት ነው።

የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት የምትባለዋና ዛሬም ድረስ ከኢትዮጵያ ጋር የጂኦ ፖለቲካ ፍጥጫ የቀጠለችው ግብፅ፣ ከራሷ አልፋ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች የሚሠሩ ሚዲያዎችን ከከፈተች ከ50 ዓመታት በላይ እንዳስቆጠረች መረጃዎች ይጠቁማሉ። እ.ኤ.አ. ከ1960 ጀምሮ የሬዲዮ ጣቢያዎች በኦሮሚኛና በሶማሊኛ ቋንቋዎች በግብፅ መከፈታቸውን ከዓመት በፊት በጉዳዩ ዙሪያ ሰፊ ዘገባ ይዞ የወጣው አል ሞኒተር የዜና ምንጭ ያመላክታል።

ግብፅ ይህንኑ እኩይ ተግባሯን በአሁኑ ወቅት አጠናክራ ለመቀጠል እንደምትፈልግ የሚገልጸው አልሞኒተር፣ በናይል ተፋሰስ አገሮች ቋንቋዎች የሬዲዮ ሥርጭቶችን ለማስፋፋት ሰፊ ሥራ እያከናወነች መሆኗን፤ «በአሥር ሬዲዮ ጣቢያዎች ሰባት የአፍሪካ ቋንቋዎችን ጨምሮ በ23 ቋንቋዎች» ለዓባይ ተፋሰስ አገሮች ሥርጭት የሚያደርሱ የሬዲዮ ጣቢያዎችን እያቋቋመች ነው» መሆኑንም፣ ከእነዚህ አገሮች ውስጥም ኢትዮጵያ እንደምትገኝና አማርኛና ኦሮሚኛን የመሳሰሉ ቋንቋዎች የፕሮጀክቱ አካል መሆናቸውን ጠቁሟል።

ይህን የግብፅ ዘመቻ ለመመከት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙኃን እና የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ትልቅ የቤት ሥራ እንደሚጠብቃቸው ለመገመት የሚከብድ አይደለም። ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠርም ወሳኝ ሀገራዊ ጉዳይ ስለመሆኑ መካሪ እና ተመካሪ የሚፈልግ አይደለም።

በተለይም የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን በዓረብኛ ቋንቋ ተደራሽነታቸውን በማስፋት ከአጀንዳ ተቀባይነት ወደ አጀንዳ ሰጪነት መሸጋገር አለባቸው። በዜጎች የግል ተነሳሽነት የሚደረጉ ጥረቶች እውቅና ሊሰጣቸው፣ ሊበረታቱ፤ አስፈላጊው የሎጂስቲክ ድጋፍ ሊደረግላቸውም ይገባል።

እንደ ሀገር ለሚያጋጥማት መሰል ችግሮች የሚዲያ ምላሽ አሰጣጥ ምን ይሁን ለሚለው መሠረታዊና ተጨባጭ መፍትሔ ማፈላለግ ላይ መሥራትም ያስፈልጋል። በብዙ መልኩ ከድህነት ለመውጣት የምናደርጋቸው ጥረቶች በአሉታዊ የሚዲያ ዘመቻ በብዙ ጫናዎች ውስጥ እየወደቁ ስለመሆኑ ያለፉትን አምስት ዓመታት የለውጥ ጉዟችንን መመልከት በራሱ በቂ ነው ።

ይህ ሁሉ ጫና የተፈራረቁት ለኢትዮጵያ አስከፊ ሊባል በሚችለው በዚህ ወቅት፣ በተለይም በግብፅ በኩል የነበሩ የማፊያ ጫናዎችን ለመከላከል ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነ ዜጎች በግል ተነሳሽነት የሀገራችንን ጥቅም ለማስከበር ተንቀሳቅሰዋል። በዓረብኛ ቋንቋ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች እየቀረቡ ስለኢትዮጵያ ጥቅሞች በመሞገት በተጨባጭ የሚታይ ለውጥ ለማምጣት ጥረት አድርገዋል። የሚታይ ስኬትም አስመዝግበዋል።

የነዚህ ጥቂት ዜጎች ጥረት፣ በፖሊሲና በስትራቴጂ ብንደግፈው ደግሞ ትልቅ ውጤት ማምጣት እንደሚያስችለን ለመገመት የሚያስቸግር አይደለም። ለዚህም አቅሙና ብቃቱ ያላቸው ለቋንቋውም ለቴክኖሎጂውም ቅርብ የሆኑ ወጣቶች በብዛት መልምለን ተገቢውን ሥልጠና ሰጥተን ወደ ሥራ ማስገባት ብዙም የሚከብደን አይሆንም።

በነዚህ ዓመታት ሀገራችን ከነበረችበት አጣብቂኝ አኳያ ለውጭ ሚዲያዎችም ሆነ ለውጭ መንግሥታት የዲፕሎማሲና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በተደራጀ መንገድ ጠንካራ ምላሽ ለመስጠት ብዙ ፈተና ቢገጥማትም፣ ችግሩን አሸንፎ ለመውጣት ዜጎች በማኅበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በስፋት ማሰማት የቻሉበት አጋጣሚ እንደነበርም ማስታወስ ተገቢ ነው።

በቅርብ ጊዜያት መፈጠር የቻሉት የ”No More” ዘመቻና ሌሎችም ጥረቶች በውጭ የሚዲያና የዲፕሎማሲ ጫናዎች ቁጭት፣ በአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ግለሰባዊ ተነሳሽነት የተወለዱ ነበሩ ማለት ይቻላል። ለዚህ ሥራ ፊር ቀዳጅ መሆን የነበረባቸው ተቋማት አልነበሩም ወይ? የሚለውም ሆነ በግንባር ቀደምትነት ኃላፊነቱን መሸከም የሚገባቸው አካላት የሉም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳቱ በብዙዎች እምነት አሁን ጊዜው ላይሆን ይችላል። ጥያቄው ቢዘገይም ተገቢ ነው ባይ ነኝ፤ ከትናንት ስህተቶቻችን ተምረን ዛሬ ላይ የተሻለ ሥራ ለመሥራት የተሻለ ዕድል ሊፈጥር የሚችል ይመስለኛል።

በአሁነኛው የዲጂታል ዘመን አንድ ሀገር ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥቅሞቿን ለማስጠበቅ ከመደበኛ የዲፕሎማሲ ሥራዎች እኩል የዲጂታል መገናኛ ብዙኃንን/ትዊተር፣ ፌስቡክ፣...ወዘተ/ በመጠቀም የዲጂታል ዲፕሎማሲ መሥራት የተለመደና ውጤታማነቱ የተረጋገጠ ነው።

ሰጥቶ መቀበልና ተግባብቶ መኖርን በሚጠይቀው የዓለም ዲፕሎማሲ መድረክ ላይ ሌሎችን ለማድመጥ ብቻም ሳይሆን፣ ተደማጭነትን ለማግኘት የዲጂታል ዲፕሎማሲ ከፍተኛ ሚና አለው። ዲጂታል ዲፕሎማሲ መደበኛ ዲፕሎማሲን አይተካም፣ የዲፕሎማሲ ተዋንያን በጨመሩበትና የመንግሥታት ግንኙነት በሰፋበት በዚህ 21ኛው ክፍለ ዘመን መደበኛ ዲፕሎማሲ በዲጂታል ዲፕሎማሲ ሊታገዝ እንደሚገባው ግልፅ ነው።

ስለኢትዮጵያ በተለይም በዓረብኛ ቋንቋዎች የሚሰራጩ ሚዲያዎች ላይ እየቀረበ የሚሟገተው መሐመድ አልአሩሲ በአንድ ወቅት «ኢትዮጵያ የውጭ ሚዲያዎች አጀንዳ ተቀባይ ሳትሆን የራሷ አጀንዳ ሰጪ መሆን አለባት» ብሎ ነበር። ይህንን በመንተራስ ግብፆቹ ኢትዮጵያን ለመጫን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሲንቀሳቀሱ መቆየታቸውን በመጥቀስም ኢትዮጵያውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ምክር ሰጥቷል።

በምክሩን «እነሱ ለረዥም ጊዜ በመደራጀት ይበልጡናል። እኛን ለረዥም ጊዜ በሚዲያ የማጥቃት ሥራም ሠርተዋል። ነገር ግን እኛም አስበንበት ከተነሳን ጥቃታቸውን መመከት እንችላለን። ትንሽ የምንሆን ልጆች በዓረብኛ ሚዲያዎች ላይ እየገባን መልስ መስጠት በመቻላችን በአጭር ጊዜ ብዙ ለውጥ መጥቷል። በቀጣይ አቅማችንን አስተባብረን ከሠራን ደግሞ በሀገራችን ላይ የደረሰውን አደጋ ማስቆም እንችላለን። ዜጎች በራስ ተነሳሽነት ስለአገራቸው ጥብቅና መቆማቸውን በተደራጀ መንገድ መቀጠል አለባቸው» ብሏል ።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያውያን አጀንዳ ተቀባዮች ሳንሆን አጀንዳ ሰጪዎች መሆን ይገባናል። እኛ እነሱ ምን አሉ ስለሚለው ጉዳይ ትተን ስለራሳችን በራሳችን መንገድ መዘገብ መጀመር ይኖርብናል። ሌሎች አገሮች ሚዲያን የዲፕሎማሲና የፖለቲካቸው ዋና መገልገያ እንዳደረጉት ሁሉ እኛም እንችላለን አቅሙም አለን።

የሌሎች ሚዲያዎችን ሴራ በንቃት መከታተል አስፈላጊ ነው። ሲኤንኤን፣ ቢቢሲና ሌሎች የምዕራባውያን ሚዲያዎች ለራሳቸው ጥቅም ያጋደሉ አሠራሮችን እንደሚከተሉ ሁሉ ሳናውቀው የእነሱ ሰለባዎች እንዳንሆን የመረጃዎቻቸውን ተዓማኒነት መመርመር ይገባናል። በዚህ ረገድ ምሑራን ወደ መገናኛ ብዙኃን በመቅረብና በተለያዩ ቋንቋዎች የኢትዮጵያን እውነት በማሳወቅ በኢትዮጵያ ላይ የሚደረገውን የሚዲያ ጫና መመከት ይጠበቅባቸዋል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

## መሬት ለመሰረተ ልማት!

**ዘካርያስ ዶቢ**

ከተማን ከተማ የሚያደርጉት ሕንጻዎች ብቻ አይደሉም፤ እንደ መንገድና የመሳሰሉት መሰረተ ልማቶችና አረንጓዴ ስፍራዎችም ስለመሆናቸው የከተማ ልማት ባለሙያዎች ይገልጻሉ።የከተሞች ማስተር ፕላንም ይህን ታሳቢ ተደርጎ እንደሚዘጋጅ ይታሰባል።አዲስ አበባም በእዚህ መልኩ ማስተር ፕላን እየተዘጋጀላት ስትገነባ ኖራለች፡፡

ይሁንና ማስተር ፕላኑን መሬት ላይ ከማሳረፍ አኳያ ሲታይ ከተማዋ በመሰረተ ልማትም ሆነ በአረንጓዴ ሽፋን በኩል ስትታይ የመሰረተ ልማቶቹ ድህነት በእጅጉ የጸናባት ሆና ኖራለች።በከተማዋ መሬት አስተዳደር ይሁን በሌላ በሚመለከተው አካል በኩል የከተማ መሬትን አስመልክቶ ለረጅም ጊዜያት ተንሰራፍቶ የቆየው አመለካከት ከሕንጻና ሕንጻ ጋር ብቻ የተያያዘ ነው ማለት ይቻላል።በከተማዋ የተካሄደው ግንባታም ሲታይ ይህንኑ ያመለክታል፡፡

ለከተማ መሰረተ ልማት እንዲሁም ለአረንጓዴ ስፍራ ልማት ግንባታ የተከለለ መሬት በሙሉ ሊያሰኝ በሚችል መልኩ ለሕንጻ ግንባታ እንዲውል ተድርጓል።ከተማዋ ኮንክሪት በኮንክሪት ለመሆን ተገዳ ቆይታለች።የቀደሙት የከተማዋ አስተዳዳሪዎች የከተማዋን መሬት ለሕንጻ ግንባታ ብቻ ማዋላቸው አልበቃ ብሏቸው መንግስታዊ ተቋማት ባላቸው ራእይ መሰረት ይዘውት ከነበሩት መሬት ላይ ጭምር ወስደው ለባለስልጣናት ያድሉም ነበር።አሁንም ቢሆን በጋራ መጠቀሚያ መንደሮች ለተለያዩ መሰረተ ልማቶች በሚል የተተው ቦታዎች ለሌላ ዓላማ እንዲውሉ ሲደረግ እየተደረገ ነው፡፡

ግንባታ ያልተካሄደበት ቦታ በኪስ ቦታነት ተይዞ በውድ ዋጋ ሲቸበቸብ ኖሯል፤ ለቦታ ጠያቂዎች መሬት ለመስጠት ከተማ አስተዳደሩ መሬት ይኑረው አይኑረው የማያውቅበት ሁኔታም ነበር።ኪስ ቦታ ጠቁሙ እየተባለ መሬት ይሰጥ ነበር።የትኛውም አይነት መሬት ሲገኝ/ብቻ መሬት ይሁን እንጂ/ የወንዝ ዳርቻዎችም ጭምር በሊዝ ተሸጠዋል።ልብ በሉ እንግዲህ ሕንጻዎችን የሚገነቡ አካላት ግንባታዎችን ከወንዞች የተወሰነ ሜትር /25 ሜትር መራቅ አለባቸው ሲባል ሰምቻለሁ/ መራቅ ያለባቸው ስለመሆኑ በሚገባ እየታወቀም ወንዝ እና ገደል አፋፉ ላይ ያለን ቦታ ሳይቀር ሕንጻ እገነባበታለሁ ላለ አካል መምራት በተለመደበት ከተማ ውስጥ ቆይተናል፡፡

በማስፋፊያ ቦታም ቢሆን ግንባር ቦታ በሊዝ ለመሸጥ ይዘጋጃል።በራቸው ላይ ሰንጋ በሬ አስረው ሲያቁለጨልጩ እንደሚከርሙ ስጋ ቤቶች ባለቤቶች ሰፋፊ መሬቶች ፊት ለፊት ላይ ክፍት ተትተው ዓመታትን እንዲቆጥሩ ሲደረግ ቆይቷል።ሌሎች ሕንጻዎች ከጀርባቸው ተሰርተው አካባቢውን ከተማ ካደረጉ በሁዋላ ለባለሀብቶች ወይም ብር ይዘው ለሚመጡ አካላት ይተላለፋሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ ነባሩ ክፍል/መሀል ከተማ ተብሎ የሚታወቀው አካባቢ/ ባለው የመሬት አስተዳደር አሰራር መሰረት የከተማዋን ደረጃ የማይመጥኑ መኖሪያ ቤቶችን፣ ድርጅቶችን ወዘተ ተሸክሞ እንዲቆይ ተደርጎ ኖሯል፤ እነዚህ ይዞታዎች በተለይ የቀበሌ ወይም በመንግስት ይዞታ ስር ያሉት ወይ አይለሙ፣ ወይ አይፈርሱ ደክመው ከተማዋን ሲያደክሟት ቆይተዋል።የግል ይዞታዎች ወይ በባለቤቶቻቸው አልያም በገዟቸው አካላት ፈርሰው የሚሰሩበት ሁኔታ ብዙ ቢሆንም፣ ካለው የግል ይዞታ ብዛት አኳያ ሲታይ የለሙት እጅግ ጥቂት የሚባሉት ናቸው።ከእዚህ የከተማዋ ክፍል ይልቅ ማስፋፊያ አካባቢዎች ይበልጥ ከተማ ከተማ የሚያውዱበት ሁኔታ ይታያል፡፡

የኮሪደር ልማቱ ለእዚህ ሁሉ የከተማዋ ችግር መፍትሄ ይዞ መጥቷል።ልማቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የታየውም ይሄው ነው።የኮርደር ልማቱ እነዚህን የከተማዋን ገጽታ ያበላሹ ግንባታዎችን በሙሉ /ለባለ ይዞታዎች ቦታና ካሳ እየሰጠ፣ ለተከራዮች የኪራይ ቤትና የመሳሰለውን እያቀረበ/ እያነሳ ይገኛል።ልማቱ ግንባሩን ብቻ ሳይሆን ገባ እያለም ሰፊ ቦታዎችን እያጸዳ ነው። ለልማቱ ያስፈልጋሉ በተባሉ ቦታዎች ላይ የተጀመሩ የትላልቅ ሕንጻ ግንባታዎች ሳይቆሩ ተሰርዞ ቦታዎቹ ለኮርደር ልማቱ ዓላማ እንዲውሉ ተደርጓል።

በዚህም ከተማ አስተዳደሩ ሰፋፊ ቦታዎች ማግኘት ችሏል።ከእነዚህ ቦታዎች መካከል እስከ አሁን የከተማ አስተዳደሩ ወደ ግሉ ዘርፍ በጨረታም ይሁን በሌላ መልክ ያስተላለፋቸው ቦታዎች አሉ ሲባል አልሰማሁም።ከዚህ ውጪ ግን የከተማ አስተዳደሩ ቦታዎቹን ከተማዋን በእጅጉ ለራባራትና ለጠማት ልዩ ልዩ መሰረተ ልማት ግንባታ እያዋለ ይገኛል።

እነዚህ ቁልፍ በሚባሉ የከተማዋ አካባቢዎች ላይ የተገኙ ቦታዎች ለሕንጻና ለመሳሰሉት ግንባታዎች በጨረታ ቢቀርቡ የከተማ አስተዳደሩን ኃላፊዎች እጅ ስመው ከተጠራው ዋጋም በላይ አስበልጠው ሰጥተው ሊገዙ የሚችሉ በርካታ ባለሀብቶችና ባለገንዘቦች ሞልተዋል። ከተማ አስተዳደሩን ይህ በፍጹም አላጓጓውም።ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት ከተማ አስተዳደሩን ያሳሰበው ከተማዋ ያለባት የመሰረተ ልማት ድህነት ነውና መሬቱን ይህን ድህነት ለመቀነሱ ተግባር አውሎታል፡፡

ለእዚህም ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ ቀበና መገናኛ ያሉትን አካባቢዎች መመልከት በቂ ነው።በእነዚህ አካባቢዎች የጸዱ ይዞታዎች ወይ ለተለያዩ የመንገድ መሰረተ ልማት ስራዎች፣ አልያም ለሰፋፊ የአረንጓዴ ልማት እንዲሁም የመኪና ማቆሚያና የገበያ ማእከላት/ሞሎችን ለመገንቢያ ነው እንዲውሉ የተደረጉት።ይህ የኮሪደር ልማት በሜክሲኮ መገናኛ ኮሪደርም ልማት እየታየ ነው።

ኪስ ቦታዎችን በወረንጦ በመልቀም በሊዝ በውድ ዋጋ ሲቸበቸብ የነበረበት ሁኔታን፣ እኔ የከተማ አስተዳደሩ «መሬት ለመሰረተ ልማት» በሚል አሰራር ቀይሮታል እንድል አርጎኛል።ለእዚህም ነው መንገዶችን ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ አድርጎ መስራት የተቻለው።የመኪና መንገዶች ብቻም ሳይሆኑ በከተማዋ በውስን አካባቢዎች ብቻ ይታዩ የነበሩ የተንጠለሉ የእግረኛ መንገዶች በተለያዩ ጎዳናዎች ላይ በስፋት ማየት የተቻለውም ለእዚህ ይመስለኛል፡፡

> **ኪስ ቦታዎችን በወረንጦ በመልቀም በሊዝ በውድ ዋጋ ሲቸበቸብ የነበረበት ሁኔታን፣ እኔ የከተማ አስተዳደሩ «መሬት ለመሰረተ ልማት» በሚል አሰራር ቀይሮታል እንድል አርጎኛል።ለእዚህም ነው መንገዶችን ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ አድርጎ መስራት የተቻለው**

የመሬት አቀማመጧ ለብስክሌት አይመችም ስትባል የኖረችው አዲስ አበባ የቸርችል ጎዳናን ዳገት ጨምሮ የኮርደር ልማቱ በሚያልፉባቸው ዋና ዋና መንገዶች ሁሉ የብስክሌት መንገዶች ተገንብተው ለትራፊክ ክፍት ተደርገው ብስክሌተኞችን እየጠበቁ ናቸው።ይህም ሊሆን የቻለው አንድም በቂ የብስክሌት መሰረተ ልማት መገንባት የሚያስችል ቦታ በመገኘቱ ነው፡፡

የመንገድ ዳር አረንጓዴ ስፍራዎች ብቻ አይደለም በኮሪደር ልማቱ እየተገቡ የሚገኙት።በጣም ሰፋፊ አረንጓዴ ስፍራዎች ተፈጥረዋል።ለእዚህም የዛሬዋን ግንፍሌ ማየት ነው፤ ከአራዳ ክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ወደ ፒያሳ እየተጓዙ መመልከትም ነው።ከተማዋ ባለፉት መንግስታት በማስተር ፕላኗ ላይ የተቀመጡ በቂ የአረንጓዴ ስፍራዎች በተለያዩ ምክንያቶች እንድታጣ ብትደረግም፣ ማንም ሊገምተው ባልቻለ ጊዜና መልኩ ይህ ዘመን አረንጓዴ ስፍራዎቿን እያስመለሰላት ይገኛል።

ከተማዋ እየተስፋፋች፣ የሕዝቧም ብዛት እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ ነባሩ የከተማዋ አካባቢ በተለይ ትናንት የተፈጠሩ አንዳንድ አካባቢዎች ሳይቀሩ ከፍተኛ የትራፊክና የሕዝብ መጨናነቅ በሚታይባቸው በእዚህ ወቅት ችግሩን ቆም ብሎ በማሰብ በኮሪደር ልማት ለመፍታት መነሳት የከተማዋ መሪዎችም የፌዴራል መንግስቱም ለከተማ ልማት የሰጡትን ልዩ ትኩረትም ያመለክታል፡፡

የኮርደር ልማቱ ይዞት የተነሳው የመንገዶች ማስፋፋት፣ አዳዲስ የታክሲና አውቶብስ መጫኛና ማውረጃ ተርሚናሎችን የመገንባት ስራ የአረንጓዴ ስፍራዎችን ፣ መጸዳጃ ቤቶችን፣ መዝናኛ ስፍራዎችን የማካተት ስራ ግዙፍ እንደመሆኑ የሚያስፈልገውም ቦታ ብዙ ሊሆን እንደሚችል በማመን አሁን በተያዘው መልኩ ከተማዋን መልሶ ለማልማት እየተከናወነ ያለው ተግባር አድናቆት ሊቸረው ይገባል።

የኮሪደር ልማቱ ከተማዋን ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ በአረንጓዴ ስፍራዎች የታጀበች ያደርጋታል። በቂ የታክሲና የአውቶብስ መጫኛና ማውረጃ ያላት እንድትሆን ያስችላታል፤ ይህም በመንገድ ጥበትና በመሳሰሉት ሳቢያ እየተገፉ እየተገፉ ዳር ሲወጡ የነበሩት የታክሲ ወይም አውቶብስ ተርሚናሎችን በቅርብ ማግኘት ያስችላል፤ በአጠቃላይ የታክሲና የአውቶብስ ተርሚኖሎች ችግር በመሰረታዊነት ይፈታል።

ይህ ብቻም አይደለም ከተማ የበርካታ ግዙፍ ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያ ፓርኮች ባለቤትም እንድትሆንም ያስችላታል፤ በአራት ኪሎ፣ በፒያሳና ሰራተኛ ሰፈር የሚካሄዱትን የፓርኪንግ የገበያ ማእከላት/ሞሎች/ ግንባታዎች የሚያመለክቱትም ይህንኑ ነው። የኮሪደር ልማቱ በሚያልፉባቸው አካባቢዎች የመጸዳጃ ቤት ጥያቄ በቀጣይ አይነሳም፤ እግረኞች ዘና ብለው የሚጓዙባቸው፣ ተሽከርካሪዎች ደረጃቸውን በጠበቁ መንገዶች የሚሽከረከሩባቸው፣ አካል ጉዳተኞች ጥያቄ የማያነሱባቸው መንገዶች እየተገነቡ ናቸው።

የከተማ አስተዳደሩ ይህን ሁሉ ለማከናወን አቅዶ በመስራቱ የመሬት ጉዳይ ስራውን አላቆመውም።ይበልጥ አጠናክሮ እንዲሰራ፣ አንድም ስራ ለነገ ሳይል እንዲያከናውን አስችሎታል ባይ ነኝ።

አዲስ አበባ ከተማ የሀገሪቱ ዋና ከተማ ብቻም አይደለችም፤ የአፍሪካ ሕብረት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፣ የአያሌ ዲፕሎማቶች መገኛም ናት።እነዚህ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት ደግሞ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መቀመጫ የሆኑ የዓለም ከተሞች የሚያስፈልጋቸውን የከተማ መሰረተ ልማት በአዲስ አበባም እንዲያገኙ ማድረግ መቻል ፍላጎታቸውን ከማሟላት ባሻገር የኢትዮጵያን ገጽታ በእጅጉ ይገነባዋል።

ይህን ግዙፍ ስራ መስራት ውስጥ መግባት እንዲሁም መፈጸም መቻል ለእኔ ባለ ራእይነትን ያመለክታል።መንግስትን ያሳሰበው አሁን ያለው የከተማዋ መጨናነቅ፣ የዘመናዊ ከተማ መሰረተ ልማት ማጣቷ ብቻ አይደለም፤ መጪው ትውልድም መጪዋ አዲስ አበባ መምሰል ያለባትም ነው።

የአሁኑ ትውልድስ እየተጨናበሰም ባለው መሰረተ ልማት ሊኖር ይችል ይሆናል።መጪው ትውልድ ባለፉት መንግስታትና በአሁኑ መንግስት ጥፋት መላወሻ ማጣት የለበትም።ለሀገሪቱ ከፍታ አስተዋጽኦ እያደረጉ ያሉት የአፍሪካ ህብረት፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን እና ሌሎች አህገራዊ፣ ክፍለ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት ደረጃቸውን የሚመጥኑ አገልግሎቶችን ማግኘት መቸገርም የለባቸውም።የሀገሪቱም የአዲስ አበባም ከፍታ እየመጣ ነው።ያንን ከፍታ የሚያስተናግድ መሰረተ ልማት መገንባት ብቻ ሳይሆን መገንቢያ ሊሆን የሚችል ቦታ ማዘጋጀት መቻል በራሱ ትልቅ ስራ ነው።ይህን ማድረግ እየተቻለ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የከተማ አስተዳደሩና የፌዴራል መንግስቱ የከተማዋን መሰረተ ልማቶች ለማሟላት የያዙት ርብርብ ባለ ራእይነታቸውን ያመለክታል፤ የከተማዋን ስር የሰደደ ችግር መንግሎ መጣልንና ደረጃቸውን የጠበቁ አገልግሎቶች የምትሰጥ አዲስ አበባን እውን ማድረግን አልመው መስራታቸውና ፍሬያማ መሆናቸው አሁን ያለው ትውልድ ብቻ ሳይሆን፣ የከተማዋን ታሪክ አንብቦ የሚረዳው መጪው ትልድም የተከበረ ስፍራ ይሰጣቸዋል ብሎ መገመትም ይቻላል።የልማቱ ሀሳብ ጠንሳሾች፣ አዳባሪዎችና ተግባሪዎች አድናቆት ሊቸራቸው ይገባል።

የከተማ አስተዳደሩና የፌዴራል መንግስቱ ይህን ሁሉ መሰረተ ልማት ለመገንባት እንዲያስችል በመሬት ላይ ለተከተሉት አሰራር አድናቆቴን ሳልገልጽ አላልፍም፤ መሬትን ለመሰረተ ልማትና መሰረተ ልማት ብቻ ማዋላቸው ትልቅ ለውጥ ማምጣት አስችሏል።

መሬትን ለሕንጻና ሕንጻ መገንቢያ ብቻ ከማድረግ በመውጣት የአረንጓዴ ስፍራዎችና ዘመኑን የሚመጥኑ የገበያ አዳራሾችን /ሞሎችን/ እና የመኪና ማቆማያዎች፣ ወዘተ. የሚገነባባቸው ማድረግ መቻል ጀግንነት ነው። መሬት እንደ ትልቅ ሀብት በሚቆጠርባትና ለሀብት ማግኛ ሲውልባትም ለቆየችው አዲስ አበባ ይህን ሁሉ በአይን ስፍራ ላይ የሚገኝ መሬት ለእነዚህ መሰረተ ልማት ግንባታዎች ማዋል በእርግጥም ጀግንነት ነው።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለመግቢያ ፈተና የሚያዘጋጀው መተግበሪያ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ወጣት አማን በረከት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ ትምህርት ዘርፍ ተመርቋል። የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለመግቢያ ፈተና (Entrance exam) የሚያዘጋጅ ፈተናዎችን የያዘ "ኢትዮ ማትሪክ (Ethio Matric)" የተሰኘ የሞባይል መተግበሪያ ሰርቶ ጥቅም ላይ አውሏል።

ወጣት አማን የ12ኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት አጋጥሞት ያለፈና አሁንም አብዛኛው ተማሪ የሚያልፍበትን መንገድ አደላድሏል። ለፈተና ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች በምን ዘዴ መፍታት ይቻላል የሚለውን አእምሮው ሲያሰላስል ቆይቷል። ዩኒቨርሲቲ ከገባም በኋላ ጊዜ ወስዶ ችግሩን እንዴት መፍታት እንደሚችል በማሰብ አውጥና አውርዶ ከተማረው ትምህርት ጋር በማዋሃድ የመፍትሔ ሀሳብ ማመንጭት ችሏል። በመፍትሔውም ኢትዮ ማትሪክስ የተሰኘ መተግበሪያ መስራት ችሏል።

ወጣት አማን ዩኒቨርሲቲ እያለ ጀምሮ ሲያስበው የቆየው ቢሆንም ሀሳቡን ወደመሬት ለማውረድ ሲያስብ ብዙ ጊዜ እንደፈጀበት ይናገራል። "መጽሐፍን አንብቦ አለመጨረስ የአብዛኛው ተማሪዎች ችግር መሆኑን ተማሪም ሆኜ ጀምሮ በቅርበት ስለማውቀው ይህን ችግር በመፍታት ተማሪዎች ሁሉንም መጽሐፍ አንብበው ከመጨረሳቸው በፊት እንዴት እንዲለማመዱ ማድረግ ይቻላል የሚለውን ሳስብ የተማርኩትን ትምህርት ተጠቅሜ በሙያዬ መፍትሔ ማምጣት እንደምችል ስለገባኝ ሥራውን ጀመርኩ›› ይላል።

"ኢትዮ ማትሪክ (Ethio Matric)" ያለፉት ዓመታት የማትሪክና የመግቢያ ፈተና ጥያቄዎች ለመስራት የሚጠቅምና ለአጠቃቀም በተመቸ መልኩ የተሰራ መተግበሪያ ነው። መተግበሪያው ተግባራዊ ከሆነ አምስት ዓመታት አስቆጥሯል። ይህ መተግበሪያ ተግባራዊ ከመደረጉ አምስት ዓመታት በፊት ባሉት ሌሎች መተግበሪያዎች ላይ በአብዛኛው የሚገኙትና እንዳሉ የሚታወቀው መጻሕፍት ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት ብዙ ስለሆኑ ተማሪዎች መጻሕፍቱን አንብበው እስካልጨረሱ ድረስ ጥያቄዎች ለመስራት ስለሚከብዳቸው አንዱ ጥያቄ ሰርተው ሲከብዳቸው ተጨማሪ ሌላ ጥያቄዎች መስራት ስለማይችሉ ብዙ ጥያቄዎች ሳይሰሩ ይተውታል። እንደገና ደግሞ ካላቸው ጊዜ አንጻር ሁሉንም መጻሕፍት አንብበው ለማዳረስ የማይችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

አማን "ተማሪዎች የቱንም ያህል ተግተው ቢያነቡ በተለይ የመጨረሻዎቹን ሁለት እና ሦስት ምዕራፍ ሳይጨርሱ የመግቢያ ፈተና ይደርስባቸዋል። ስለዚህም የፈተናዎቹን ጥያቄዎች መስራት እያለባቸው ይህንን ምዕራፍ ጨርሼ ሰራዋለሁ እያሉ ሲዘናጉ የሚፈልጉትን ማዳረስ ሳይችሉ ጊዜው ስለሚያጥራቸው ፈተናውን ሳይሰሩት ይቀራሉ›› ይላል።

ታዲያ ይህ መተግበሪያም ተማሪዎች የሚያጋጥማቸው ችግር ለመፍታት መጻሕፍቱን በየምዕራፍ በመከፋፈል በየእያንዳንዱ ምዕራፍ ያሉ ጥያቄዎችን በተደራጀ መልኩ በማቅረብ መስራት የሚችሉበት መንገድ ቀርቧል። ብዙ ተማሪዎች ሁሉንም መጻሕፍት የማዳረስ እድላቸው አነስተኛ ስለሆነ ካነበቡት መጻሕፍት ጎን ለጎን አንዱን ምዕራፍ ሲጨርሱ ጥያቄዎች እዚያ በመስራት ያሉበት ሁኔታ እየፈተሹ ማሻሻል የሚገባቸው እያሻሻሉ እንዲሄድ ይረዳቸዋል።

መተግበሪያው በሞባይል የሚሰራ ሲሆን በሞባይል እንዲሆን የተደረገበት ዋንኛ ምክንያት በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የትምህርት አሰጣጥ የዲጂታል አሠራር የተከተለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ነው። አብዛኛው ተማሪዎች ሞባይል ያላው በመሆኑ ሥራውን ቀላል ያደርገዋል። ሞባይል የሌላቸው ጥቂት ተማሪዎች ቢኖሩም ከወላጆች አልያም በቅርበት ካሉ ሰዎች ሊያገኙ ስለሚችሉ መተግበሪያውን አውርደው መጠቀም የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይችላሉ የሚል እምነት እንዳለው ይናገራል።

መተግበሪያው ባለፉት ስምንት ዓመታት የመግቢያ ፈተና ጥያቄዎችን፣ ከ2008 እስከ 2015 ዓ.ም የመግቢያ ፈተናዎች፣ ጥያቄዎች በየምዕራፉ ከፍፍሎ ያስቀመጠ እና ለጥያቄዎቹ ማብራሪያ ያካተተ ነው። መተግበሪያው ጥያቄዎች እና መልሶቻቸውን የያዘ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ማብራሪያ ይሰጣል። ለምሳሌ አንድ ጥያቄ ከጠየቀ በኋላ ለዚያ ጥያቄ የሚሆን የተሻለ ማብራሪያ የሚሰጥ በመሆኑ ተማሪ ጥያቄውን ከመመለስ ባሻገር ስለጥያቄ በደንብ እንዲያውቅ፣ እንዲረዳና እንዲገነዘብ ይረዳዋል።

ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከማትሪክ ጥያቄ ጎን ለጎን የመግቢያ ፈተና ጥያቄዎች መስራት ጠቃሚ መሆኑን ተማሪዎች በሚገባ ያውቃሉ የሚለው ወጣት አማን፤ ለዚህም ነው በመተግበሪያው ሁለቱን በአንድ ማካተት ያስፈለገው ይላል። አብዛኛው ትኩረት ያደረገባቸው ግን የባለፉት ዓመታት የመግቢያ ፈተና ጥያቄዎች ላይ ነው። ከዘንድሮ ዓመት ጀምሮ የተለያዩ አዳዲስ ነገሮችን ለማካተት ማሰቡንም አጫውቶናል።

ወጣት አማን እንደሚለው፤ ምንም እንኳን መተግበሪያ ተግባራዊ ከሆነ አምስት ዓመታት የተቆጠሩ ቢሆንም በተለይ ከሁለት ዓመታት ወዲህ ግን ትላልቅ የሚባሉ ማሻሻያዎች ተደርገውበታል። መተግበሪያው ይበልጥ እየታወቀ የመጣው ደግሞ ከሁለት ዓመታት ወዲህ ነው ብሏል። እሱ እደሚለው እስካሁን ድረስ መተግበሪያውን እየተጠቀሙ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር እጅግ በርካታ ሲሆን፤ አሁን ላይ ባለው መረጃ መሰረት ከ390 ሺ በላይ የሚሆን ተጠቃሚዎች መተግበሪያውን አውርደዋል። በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ያሉ ተማሪዎችም እንዲሁ የመተግበሪያው ተጠቃሚ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ።

መጀመሪያ ላይ መተግበሪያ ተግባራዊ እንደተደረገ ተማሪዎች ወዳሉበት አካባቢዎች በአካል በመሄድ ስለ መተግበሪያ ያላቸው አስተያየት እንዲሰጡት ይጠይቅ እንደነበር የሚያስታወሰው አማን፤ በወቅቱ የመተግበሪያው ተጠቃሚዎች በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም እነርሱ በሰጡት አስተያየት መሠረት የተለያዩ ማሻሻያዎችን ማድረግ እንደቻለ ተናግሯል። በማሻሻያው ቀደም ሲል ያልተካተቱ እንዲካተቱ ሆኖ መተግበሪያው አሁን የያዘውን ይዘት እንዲኖር ተደርጓል ሲል ያስረዳል።

"አሁን ላይ የመተግበሪያው ብዙ ተጠቃሚዎች ተማሪዎች ስላሉ በቴሌግራም እና በስልክ ጭምር ግንኙነት እናደርጋለን። በመተግበሪያው ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችም በመተግበሪያ ላይ የብዙ ዓመታት ጥያቄዎችን ከነማብራሪያቸው ማግኘት እንደቻሉና ብዙ ለማወቅ እንደረዳቸው በመግለጽ ይህንን ቢጨምር ወይም ደግሞ በዚህ መልኩ ቢሻሻል የሚሉትን ሀሳብ እየሰጡን ነው። በዚህም መነሻነትም በሚቀጥሉት ጊዜያት በየጊዜው ብዙ ነገሮች በማሻሻል አዳዲስ ነገሮች በመጨመር ተመራጭ መተግበሪያ እንዲሆን በማድረግ ለተማሪዎች መተግበሪያ ተጠቅመውበት የተሻለ ውጤት የሚያመጡበት እንዲሆን እፈልጋለሁ" ይላል።

መተግበሪያ ሲሰራ ሀሳብ አመንጭቶ የሰራው አማን ቢሆንም አሁን ላይ ግን በብዙ ባለሙያዎች በጥምረት እየተሰራ ይገኛል። ብዙ የሶፍትዌር ዴፕሎፐሮች፣ የእያንዳንዱ ትምህርት ዘርፍ መምህራን እና ሌሎች አጋር አባላትም በአንድ ላይ የሚሰሩበት ነው። በተጨማሪም የሚሰራው ሥራው እንደወቅቱ የሚለያይ ሲሆን ሥራው በሚኖርበት ወቅት እንደየአስፈላጊነቱ ብዙዎችን ያሳትፋል። ለአብነትም መግቢያ ፈተናዎችን መስራት ሲያስፈልግ ከየትምህርት ዘርፉ የተውጣጡ መምህራን እንዲሳተፉ ተደርጎ ይሰራል ሲል ያብራራል።

**ይህ መተግበሪያ እንደቲክቶክና ቴሌግራም ያሉ የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የማስተዋወቅ ሥራዎች ተሰርቷል፤ እየተሰራም ነው**

መተግበሪያውን ጭኖ ለመጠቀም የሚፈልግ ተጠቃሚ እስካሁን ባለው አሠራር ለአገልግሎቱ የተቀመጠውን ክፍያ እንዲከፍሉ ይጠይቃል የሚለው አማን፤ ይህም ክፍያውን በባንክ፣ በሞባይል ባንኪንግ እና በቴሌ ብር አማካኝነት ከፈጸሙ በኋላ መተግበሪያውን አውርደው መጠቀም የሚችሉበት አሠራር መዘርጋቱን ይገልጻል። በመቀጠልም የኢትዮ ማትሪክ መተግበሪያ አገልግሎቶችን ለማግኘት ተጠቃሚዎች ክፍያው ከከፈሉ በኋላ ያሉትን አገልግሎቶች ሁሉንም መጠቀም እንደሚችሉ አስገንዝቧል።

መተግበሪያው ተማሪዎችን ከመርዳት አንጻር የሚሰጠው ከፍተኛ ጠቀሜታ ሆኖ ሳለ የተቀመጠው ክፍያ በጣም አነስተኛና የተማሪዎችን የመክፈል አቅም ያገናዘበ መሆኑን ይጠቅሳል። ይሁን እንጂ መተግበሪያ እየሰጠ ካለው አገልግሎት አንጻርና አሁን ላይ እያስከፈለ ያለው ክፍያ አነስተኛ በመሆኑ በቀጣይም ከዚህ የበለጠ የተሻለ ሥራ ለመስራት ይረዳ ዘንድ ዋጋ ጭማሪ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻል። በመሆኑም በዘንድሮ ዓመት በመጠኑም ቢሆን የዋጋ ጭማሪ እንደሚያደርግ አስታወቋል።

ወጣት አማን እንዳብራራው፤ አንድ ተማሪ መተግበሪያው ለመጠቀም መተግበሪያ/ አፕሌኬሽኑን/ ጎግል ፕሌይስቶር ላይ በመግባት በማውረድና መጠቀም ሲፈልግ ለአገልግሎቱ የሚጠይቀውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ሙሉ አገልግሎት ማግኘትና መጠቀም ይችላል። ይህ ከመሆኑ በፊት ደግሞ ተጠቃሚው /ተማሪው/ የሚሰጠው የመተግበሪያ መፈተሻ እንዲኖረው ተደርጓል። ተማሪው መጀመሪያ መተግበሪያው ለማውረድ ሲገባ መተግበሪያውን አይቶት፣ ወድዶት እና መርጦት እንዲጠቀምበት ስለሚያስፈልግ ሙከራ ፈተናዎችን ያለምንም ክፍያዎች መጠቀም ይችላል። መተግበሪያ በዚህ መልኩ ከፈተሸ በኋላ መተግበሪያው ከተመቸው የሚጠበቅበት የአገልግሎት ክፍያ ከፍሎ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ይደረጋል።

ይህ መተግበሪያ እንደቲክቶክና ቴሌግራም ያሉ የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የማስተዋወቅ ሥራዎች ተሰርቷል፤ እየተሰራም ነው። በተጨማሪም መተግበሪያው በደንብ እንዲተዋወቅ ተማሪዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ መሆኑን ጠቅሶ፤ አንድ ቀድሞ መተግበሪያው የተጠቀመ ተማሪ ለሌሎች ተማሪዎች በመንገርና በመጠቆም ተማሪዎች እርስ በእርስ በሚሰጣጡት መረጃ ተደራሽነቱ እንዲሰፋ ምክንያት እየሆነ መሆኑን ተናግራል።

በቀጣይም አሁን ላይ መጽሐፉ እየተቀየር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ለተማሪዎች የማይጠቅሙ ጥያቄዎችን በመቀነስ፤ የሚጠቅሙትን ደግሞ በመጨመር እንዲበዙ የማድረግ ስራ ይሰራል የሚለው አማን፤ ተማሪዎቹ እንደዚህ አይነት የማትሪክ ጥያቄዎችና መግቢያ ፈተናዎች ቀድመው አግኝተው ከሰሩና የራሳቸውን ጥረት ካደረጉ ውጤታማ የማይሆኑበት ምክንያት እንደሌለ ይገልጻል።

ተማሪዎች የሚፈለገውን ውጤት አምጥተው ውጤታማ እንዲሆኑ ስለሚፈልግ ወደፊት ተማሪዎችን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚያስችል ሥራዎች እንደሚሰራ የሚገልጸው አማን‹‹ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ያለውን የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች እንኳን ብንመለከት ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ኢትዮ ማትሪክ የተሰኘውን መተግበሪያ ሲጠቀሙ እንደነበር አውቀናል። የሞባይል መተግበሪያው በአገሪቱ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ አብዛኛውን ጊዜ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች እንደተጠቀሙት ማወቅ ችለናል›› ይላል።

ለአብነት ሲጠቅስም ባለፈው ዓመት ከፍተኛ ውጤት ካመጡት ተማሪዎች መካካል ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ደረጃ ያለውን ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች መተግበሪያውን መጠቀማቸው ታውቋል። በዘንድሮ ዓመት ከትግራይ ክልል ከፍተኛ ውጤት ያመጣውን ተማሪ ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችም እንዲሁ መተግበሪያውን እንደተጠቀሙ መረጃዎቹ ያሳያሉ። በተጨማሪም በከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳለፍ ከሚታወቁ ትምህርት ቤቶች መካከል ለምሳሌ ኦዳ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመተግበሪያው ተጠቃሚ ነበሩ።

"ከምንም በላይ ግን የእነዚህ ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ የራሳቸው ጥረት ነው። ተማሪዎቹ መተግበሪያውን ተጠቅመው ጥያቄዎች መስራት መቻላቸው በራሱ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የራሱ አስተዋጽኦ ያበረከታል" የሚለው አማን፤

እነዚህ ተማሪዎች መተግበሪያውን ሲጠቀሙ ስማቸውና የትምህርት ቤታቸውን ስም ስለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ሲያመጡ መተግበሪያውን መጠቀማቸው እና አለመጠቀማቸው በቀላሉ መለየት ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች ራሳቸው በስልክና በቴሌግራም በኩል መተግበሪያው እንደጠቀማቸው በመናገር የሚያሳወቁበት ሁኔታ መኖሩን አመላክቷል ።

ጀማሪ ሥራ ፈጣሪ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህ መተግበሪያ ተግባራዊ እንዲደረግና ወደ ቢዝነስ እንዲቀየር በሚደረጉ ሂደቶች ጥቃቅን የሚመስሉ ተግዳሮቶች አጋጥመውት እንደነበር የሚያነሳው አማን፤ ሆኖም ግን እነዚህን መሻገርና ወደኋላ መተው ስለሚያስፈልግ በሀሳቡ ያለውን ፈጠራ ወደ ተግባር በመለወጥ ለብዙዎች መፍትሔ ሆኖ ተደራሽ እንዲሆን ጠንክሮ መስራትና ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይገልጻል። በቀጣይም ችግር ሆኖ መፍትሔ ለሚሹ ነገሮች በተማረበት የትምህርት መስክ በሙያው የሚችለው የመፍትሔ ሀሳብ በማመንጨት እንደሚሰራ ተናግሯል።

# የግብጽ እና ሶማሊያ ጥምረት - እስከ የት?

**አስቴር ኤልያስ**

ለበርካታ ዓመታት በብዙ ፈተና ውስጥ ማለፍ ግድ ብሏት ቆይታለች፤ በተለይ የሰላም እጦት ሲያንከላውሳትና ሕዝቧም ሲንገላታ እዚህ ደርሳለች። ወዲህ ሽብርና ረሃብ፤ ወዲያ ደግሞ የመበተን ስጋት ሰቅዞ እንደያዛት የዘለቀች ስለመሆኗ የአደባባይ ምስጢር ነው - ጎረቤት አገር ሶማሊያ።

በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ግን አብራት የቆመችና እንደ ሀገርም እንድትረጋጋ ጥረት ያደረገች ብቸኛ ሀገር ብትኖር ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ እንደ አንድ ጎረቤትና ወዳጅ አገር ሰላሟን ለማስከበር ጥራለች። በመሆኑም ብዙ ጊዜ እፎይታ እንድታገኝ ያደረገቻት የቁርጥ ቀን ጎረቤቷ ናት። ሰላሟን በማስጠበቅ ብቻ ሳይሆን መንግስት አልባ ሆና እንዳትፈራርስም ኢትዮጵያ የአንበሳው ድርሻ በመወጣት ረገድ ሚናዋ የጎላ ስለመሆኑ የሚታወቅ ነው።

በተለይም ጽንፈኛ አሸባሪ ቡድን አልሸባብ፣ በጉያዋ ተሸሽጎ እርሷንም ሆነ ኢትዮጵያ ጨምሮ በቀጣናው የሚገኙ ጎረቤቶቿን እንዳያስጨንቅ ኢትዮጵያ በብዙ የደከመች እና መስዋዕት የከፈለች አገር መሆኗ የሚዘነጋ አይደለም።

ጀግናው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሰራዊት ለሶማሊያ ሰላም ደሙን አፍስሷል፤ አጥንቱንም ከስክሷል፤ ሕይወቱንም ሰውቷል። ከዚህ የተነሳ አገሪቱ በፈተናዎች ውስጥ ሆናም ቢሆን እስከ ዛሬ ድረስ ሳትፈርስ እንድትቆይ ያደረገቻት አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ናት።

ይሁንና የኢትዮጵያን ማደግንም ሆነ ሰላም መሆን አጥብቃ የምትቃወም አገር ስለመሆኗ በተለይም ከሰሞኑ በአደባባይ አስመስክራለች፤ ኢትዮጵያ ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ባለቤት ሆና ሳለ፤ የባሕር በር ግን አጥታ ስትኖር መከረሟን በቅርበት ብታውቅም ከራስ ገዟ ሱማሌላንድ ጋር የባሕር በር ማግኘት የሚያስችላትን ስምምነት ባደረገች ማግስት በአደባባይ ያዙኝ ልቀቁኝ ስትል ታይታለች።

በወቅቱ የጠልፎ መጣል ሴራዋን ይዛ ወደአገረ ኤርትራ እግር አብዝታም ሰንብታለች፤ ከወዲያ በኩል ለጊዜው የፈለገችውን ያህል ምላሽ ብታጣ ደግሞ ወትሮም ቢሆን የኢትዮጵያ እድገት ወደሚያበሳጫት ግብጽ ተሻግራለች፤ ጉዳዩ በመሻገር ብቻ ያበቃ ሳይሆን ባለፈው ነሐሴ ወር የጦር መሳሪያዎችን የጫኑ ሁለት የግብጽ የጦር አውሮፕላኖች ሱማሊያ መግባታቸው አነጋጋሪ ሆኖ ሰንብቷል።

እራሷ ሰላም አጥታ ሌሎችንም ሰላም ለመንሳት የተነሳችው ሶማሊያ፣ ከግብጽ ጋር የፈጠረችው ጥምረት ኢትዮጵያ ላይ የሚያመጣው ነገር ምንድን ነው? ኢትዮጵያ በሁለቱ ጥምረት የሚደርስባት ጫና ይኖር ይሆን? ስንል የዘርፉን ምሁራን አነጋግረናል።

የውጭ ግንኙነት እና የደህንነት ቋሚ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ዲና ሙፍቲ እንደሚሉት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፤ ለጎረቤት ሀገራት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ፣ የሰከነ እና መርህን መሠረት ባደረገ በበጎ መንፈስ የተቃኘ እና ዘላቂ ዲፕሎማሲ ላይ የሚያተኩር ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ በየጊዜው ለሚሰነዘሩ ትንኮሳዎች ምላሽ የመስጠት ሂደት ውስጥ አትገባም።

አምባሳደር ዲና፣ የግብጽንና የሱማሊያን ጥምረት የሚያዩት በዓለም አቀፍ ግንኙነት መሰረት በአገሮች መካከል ያለውን አይነት ግንኙነት አድርገው ነው። ስለዚህም ለእርሳቸው የሁለቱ አገራት ጥምረት የራሳቸው የአገራቱ ሉዓላዊ መብት ነው። የትኞቹም ጎረቤት አገሮች ሆኑ በሩቅም ሆነ በቅርበት ያሉትን ጨምሮ እርስ በእርስ የሚያደርጉት ግንኙነት የራሳቸው ሉዓላዊ መብት እንደሆነ ተናግረዋል። አክለውም በሁለቱ አገራት ጥምረት ጉዳይ ኢትዮጵያ ምንም ችግር የለባትም ብለዋል።

አምባሳደር ዲና እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ ፖሊሲዋም ውስጥ የተቀመጠው ነገር የአገሮችን ሉዓላዊነት ማክበር ነው። ከጎረቤት አገራት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር ነው። ይህ ደግሞ ወዳጅነትም ነው፤ እልፍ ሲልም ትብብርም ጭምር ነው። ከተተጠቀሱት አገራት ጋር የኢትዮጵያ ፍላጎት ይኸው ነው።

የሕግ ምሁሩ፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ መስራችና ፕሬዚዳንት የሆኑት ፖለቲከኛው ተሻለ ሰብሮ (ዶ/ር)፣ የሁለቱን አገራት ጥምረት ያዩበት መነጽር ከአምባሳደር ዲና የተለየ ነው። የግብጽ የአሁኑ አስተዳደር

> “
> **አንዲት አገር ሺ ኪሎ ሜትሮችን ተጉዞ መጥታ ጎረቤት ከሆነች አገር ጋር ተጣምራ መሳሪያ ማስገባት እና አንድን አገር ለመውረር መዘጋጀት የሚወገዝና ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ነው**

ከምስራቋ ጎረቤታችን ሶማሊያ መንግስት ጋር የገባው ቃል ኪዳን የጦርነት ቃል ኪዳን ነው ማለት እችላለሁ ይላሉ።

የሁለቱ አገራት ጥምረትና መደጋገፍ በኢትዮጵያ ላይ ምን ሊያመጣ ይችላል ? የሚለውን እንደ አንድ ፖለቲከኛና የሕግ ሰው ሲመዝኑት እንደ ሕግ ሲታይ የዓለም አቀፍ ልምምድ የሚያሳየው የሁለቱ በዚያ ልክ መንቀሳቀስ እውቅና የሚያሰጠው ተግባር አይደለም ይላሉ። ፖለቲካዊውም ሆነ ዲፕሎማሲያዊ አሰራሩ በዚያ አካሔዳቸው ብዙ ጊዜ ቅቡል አይሆንም፤ ድጋፍም አያገኝም ሲሉ ያስረዳሉ።

እንደ ተሻለ (ዶ/ር) ገለጻ፤ አንዲት አገር ሺ ኪሎ ሜትሮችን ተጉዞ መጥታ ጎረቤት ከሆነች አገር ጋር ተጣምራ መሳሪያ ማስገባት እና አንድን አገር ለመውረር መዘጋጀት የሚወገዝና ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ነው። በዓለም አቀፍ መርህ ላይም ይህ አይነቱ ጥምረት ተቀባይነት የሌለው ነው። እንዲያውም ጣልቃ ገብነትም ጭምር ነው። ከዚህ የተነሳ የሚወገዝ ነው።

በእርግጥ ይላሉ ተሻለ (ዶ/ር)፣ ግብጽ በአፍሪካ ሰሜናዊ ክፍል የምትገኝ፣ ሶማሊያ ደግሞ በምስራቅ የአህጉራችን ክፍል ያለችና ኢትዮጵያን የምታዋስን ናት። ሁለቱም በኢትዮጵያ ላይ ያላቸው አመለካከት ሲሰላ ተቀራራቢ የሆነ እይታ ያላቸው አገራት ናቸው ይላሉ። እንዲያውም በእርሳቸው አገላለጽ፤ ሁለቱ አገራት በኢትዮጵያ ላይ ያላቸው ሁኔታ ሲያስረዱ፤ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው ሲሉ ይገልጿቸዋል። ሁለቱ አገራት ኢትዮጵያን መፈታተናቸው ዛሬ የተፈጠረና እንግዳ የሆነ ነገር ሳይሆን የሚታወቅና ድሮም ያለ ጉዳይ መሆኑን ያስታውሳሉ።

ተሻለ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ ግብጽ በኢትዮጵያ ላይ ስታደርስ የነበረው ተግዳሮት መልከ ብዙ ነው። ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር በኩል ምንም ሚና እንዳይኖራት በብዙ ትለፋለች። ኢትዮጵያ የተዳከመች በመሰለቻት ጊዜ ሁሉ በተላላኪዎቿ አማካይነት ድንበሯን የማስገፋት ሴራም ታሴራለች። ኢትዮጵያን ማጥቃት የምትሻው ሁልጊዜ የእርሷ መሳሪያ አድርጋ ልክ እንደ አገልጋይዋ የምትቆጥራቸውን ተላላኪዎች በመጠቀም ነው።

ኢትዮጵያ ሉዓላዊት አገር ናት፤ በአፍሪካ ምድርም ብቸኛዋ ነጻ ሕዝብና መንግስት ያላት ሆና ክብርና ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ የኖረችም መሆኗ ሁሉም የሚያውቀው ሐቅ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያን በጫና ውስጥ የማኖር ሕልሟ ፈጽሞ አይሳካላትም። በተለይም ሕልሟ ሆኖ ይቀራል እንጂ አሁን እያደረገች ባለው በሶማሊያ በኩል ምንም ልታሳካ አትችልም ይላሉ። ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የነበራት ታሪክ የሚያሳየው ለትብብርን እንጂ ለወራሪ ኃይል ቤት ለእንበሳ ብላ አታውቅም። በየትኛውም መስመርና በየትኛውም አካል ፊት አውራሪነት ለሚሰነዘርባት ትንኮሳ እራሷን ዝቅ የማታደርግ መሆኗ ከዚህ በፊትም የተረጋገጠ ስለመሆኑ ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ የራሷን ሉዓላዊነት ማስከበር ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የምትደርስ አገር ናት የሚሉት ፖለቲከኛው ተሻለ (ዶ/ር)፣ ለሶማሊያ መንግስትም ሆነ ለሶማሊያ ሕዝብ እፎይታንና መረጋጋትን የፈጠረች አገር ናት ይላሉ። ለሶማሊያ አለመበታተን የእኛው ሰራዊትና የዲፕሎማሲያዊ ድሎች ውጤት ያመጣው በጎነት እንደሆነም ያመለክታሉ። እንደሚታወቀውም ከአምስት እስከ አስር ሺ የሚሆኑ የኢትዮጵያ ወታደሮች ደማቸውን አፍስሰዋል፤ እያፈሰሱም ነበር። የሶማሊያን መንግስት ሕልውና አስጠብቀው እየኖሩም ነበር። ለሶማሊያ ሉዓላዊነት ሲባልም በአልሸባብና በሌሎች ሽብርተኞች እየተቀጠፈ ያለው ኢትዮጵያዊ ሆኖ ሳለ፤ በዚህ ድርጊታችን እኛ ኢትዮጵያውያን ክብርና ሙገሳ ሲገባን፣ ምስጋና ጭምር ሲገባን፣ ውለታም ሊዋልልን ሲገባን በተገላቢጦሹ «ባጎረስኩኝ ተነከስኩኝ» ሆኖብን አረፈው ይላሉ።

ፖለቲከኛው እንደሚናገሩት ከሆነ፤ የሶማሊያ ስደተኞች በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ። ኢትዮጵያም እነዚህን የሶማሊያ ዜጎች የባይተዋርነት ስሜት እንዳይሰማቸው እንደዜጎቿ አድርጋ ይዛ በመኖር ላይ ናት። በዚህም እንክብካቤ ውስጥ ሆናም አንድነትን ጠብቃ የዘለቀች አገር ናት። እነዚሁ ሶማሊያውያን በኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው እየነገዱ ሕይወታቸውን የሚመሩም ጭምር ናቸው። ይህም የኢትዮጵያን አቃፊነት የሚያሳይ ነው ይላሉ።

አምባሳደር ዲና በበኩላቸው እንደሚያብራሩት የሁለቱ ጥምረት ቀይ መስመር የሚሆነው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ የተቃጣ ከሆነ ብቻ ነው። አሁን የምንሰራው እንደ ኢትዮጵያ፣ እንደ መንግስትም ሆነ እንደ ሕዝብም ትኩረት መደረግ ያለበት ማንኛውም ክስተት ዓለም አቀፍ ግንኙነትም ይሁን አህጉራዊ ግንኙነቶች እንዲሁም በየነ መንግስታት ግንነኙቶች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ እንዳያነጣጥሩ ብቻ ነው ይላሉ።

የተጠቀሱትን ሁለቱን አገሮች ለየት አድርገን ካየነው የቅርብ ጊዜ ግኑኙነት ምንድን ነው? ሁለቱ የሚሰጡት መግለጫዎች ምንድን ናቸው? እየተሰሙ ያሉ መረጃዎችስ ምንን ያስተላልፋሉ? የሚሰጡ አስተያየቶች እና ትንተናዎች ምንድን ናቸው? የሚል ነው ያሉት አምባሳደር ዲና፣ ከእነዚህ ከተጠቀሱት አገሮች አካባቢ ያሉት በአመራር ላይ ያሉትም ሆነ የሌሉት ግን ደግሞ ምሁራን የሚባሉት ሁሉ አንዳንዶቹ የሚሰጡት አስተያየቶች አፍራሽ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህን በጥርጣሬ እንዲታይ የሚያደርግ ነው ይላሉ።

አምባሳደር ዲና እንደሚሉት፤ ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳርፍ ኢትዮጵያ ዲፕሎማሲዊ ጥረት ታደርጋለች። የሶማሊያ ሕዝብ ትልቁ የቅርብ ወዳጅ የሆነውና በአካባቢው ካለው ሕዝብ ቀዳሚ የሚያደርገው ኢትዮጵያን ነው። ምክንያቱም ሶማሊያ ችግር ላይ በወደቀችበት ሰዓት ለሶማሊያ ሉዓላዊነት፣ ሰላምና መረጋጋት በግንባር ቀደምትነት በሁሉም መስኮች ሕይወት ጭምር በመክፈል የታገለችው አገር ኢትዮጵያ ናትና ነው። ስለዚህ ከሶማሊያ ጋር ምንም አይነት ችግር የለንም ሲሉ ይናገራሉ።

ነገር ግን ይላሉ አምባሳደር ዲና፣ የሌሎችን አጀንዳ ተሸክመው በሱማሊያ ስም በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ ለማሳረፍ የሚችሉ ጥቂት ወገኖች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመት ሞኝነት አይሆንም። ስለዚህም ትኩረት ሰጥቶ መታገል የሚገባው በዚህ ጉዳይ ላይ ነው ይላሉ። ስለሆነው የሁለቱ አገሮች ጥምረት የተባለው አደጋ መቀመጥ ያለበት በዚህ ደረጃ ነው ባይ ናቸው።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ ዝም ብላ ዱላ አንስታ ዘራፍ ብላ የምትፎክር ሳይሆን ሁሉንም በልኩ ገምታ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ማድረግን ትቀጥላለች። ከሁለቱ አገራት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በወዳጆቻቸው በኩል ይህ ነገር እንደማያወጣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት መጻረር በፍጹም የሁለቱን አገሮች ጥቅምን እንደማያራምድ ማሳየትን ይጠይቃል ማለት ነው። ትልቅ ጥረት ማድረግ የሚጠበቅብን በዚህ በኩል ነው።

ተሻለ (ዶ/ር)፣ በአገራቱ አማካይነት የቱንም ያህል ጥምረት ይደረግ እንጂ እኔ ምንም አይነት ጉዳት በኢትዮጵያ ላይ ይደርሳል የሚል ሐሳብ የለኝም የሚሉት ፖለቲከኛው ተሻለ (ዶ/ር)፣ የለየለት ጦርነት ይካሔዳል ብዬ መናገር አልችልም ብለዋል። ለዚህ ምክንያታቸው ሲያስቀምጡ ደግሞ ጦርነቱ ሊጀመር የነበረበት አጀንዳ የከሸፈና እየከሸፈ ያለ በመሆኑ ነው ይላሉ።

ደግሞም ኢትዮጵያ የሽንፈት ታሪክ እንደሌላትም አስታውሰው፤ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ያለው ዲፕሎማሲ አካሔድም ጥበብ የተሞላበት በመሆኑ እና ታላቅ ስራም እየተሰራበት ያለ መሆኑ ከበባውን ከወዲሁ የሚበትን አካሔድ ነው የሚል እምነት አለኝ ሲሉ ያስረዳሉ።

ስለዚህ አሁን መጨረሻ ላይ የማየው ነገር ቢኖር “የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች” እንዲሉ በኢትዮጵያ ላይ እንዘምትና እናምበረክካታለን ብለው መተባበራቸው ለየራሳቸው ውድቀትን የሚያመጣባቸው ነው ይላሉ። በተለይም ሶማሊያውያን በራሳቸው የጎሳ ፖለቲካ ውስጥ ገብተው እንደተለመደው እርስ በእርስ መባላት ብቻ ሳይሆን መፈራረስም ሊያጋጥማቸው ይችላልና ጥንቃቄ የተሞላበት አካሔድ ቢከተሉ መልካም ነው ሲሉ ገልጸዋል። ብዙዎቹ ሶማሊያውያን ፍትህን በመፈለግ ከኢትዮጵያ ጋር በሰላም ለመኖር የወሰኑ መሆናቸውም ሊሰመርበት እንደሚገባ አመልክተዋል።

ኢትዮጵያን እንወጋለን ብለው ራሳቸው ምናልባት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተበታትነውና ፈራርሰው ሊቀሩ ይችላሉ የሚል አተያይ አለኝ የሚሉት ተሻለ (ዶ/ር)፣ ይህን የማይፈልጉ ሌሎች የነጻነት ታጋዮች የሆኑት ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር ተባብረው ለመስራት ወደ ውሳኔ ይመጣሉ ብዬ አምናለሁ ብለዋል። ስለዚህ ብዙ አይነት ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ስላሉ፤ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ስራዎች እየተሰሩ ስለሆነም በእኛ በኩል የእኛ መንግስት በጣም በሚደነቅ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል ሲሉ ጠቅሰዋል። በሁሉም አካባቢዎች ላይ ሁለንተናዊ ጥንካሬያችንን ይዘን መቀጠልና መቆየት የተሻለ አካሔድ መሆኑን ተናግረዋል።

አምባሳደር ዲና በበኩላቸው የኢትዮጵያን ጥንካሬ ሲያስታውሱ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷንና ነጻነቷን የመጠበቅ ሰፊ እና ረጅም ታሪክ ያላት ሉዓላዊት አገር ናት። ሕዝቦቿ በነጻነታቸው ቀና ያሉ ናቸው። ከሉዓላዊነታቸው ጎንም የሚቆሙ ናቸው። ከዚህ ቀደምም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ነጻነት የተጻረረ ማንኛውም ወገን አልተሳካለትም፤ የተመለሰውም አፍሮ ነው።

አሁንም ቢሆን በዚህ ደረጃ የሚመጡ ኃይሎች ካሉ እነዚህን ኃይሎች ለመመከት ሕዝቡ አንድነቱን ጠበቅ አድርጎ፣ አይኑንም አቅንቶ 24 ሰዓት ሉዓላዊነቱን መጠበቅ አለበት። መንግስትም አመራር የሚሰጠው ቀይ መስመር እንዳይታለፍ ነው፤ የሁለቱ አገራት ግንኙነት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትላይ ኪሳራ እንዳይሆን በንቃት መጠባበቅን ይጠይቃል ብለዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰሞኑን በሰጠው መግለጫውም እንዳለው፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ከቅርብ ጎረቤቶቿ ጋር የሚደረጉ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶችን በቅርበት ትከታተላለች። አስፈላጊ በሆነበት ጊዜም ተገቢውን ምላሽ ትሰጣለች።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ሴቶችን የማብቃት ጅማሮ በጋምቤላ ክልል

**አመለወርቅ ከበደ**

የጋምቤላ ክልል ኢትዮጵ ውስጥ ከሚገኙ ክልሎች በተለያዩ ግዜያት ጎርፍና ሌሎች ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የሚያጋጥሙት ክልል ነው።በዚህም በርካታ ሰዎች በየግዜው ተፈናቃይ ይሆናሉ፡፡በዚህም ሴቶችና ሕጻናት የመጀመሪያዎቹ ተጎጂ ናቸው፡፡

በባህላዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ለተለያዩ ችግሮች የሚጋለጡትን የክልሉን ሴቶች ለመታደግ በርካታ ስራዎች ሲከናወኑ ለማየት ችለናል።ከእነዚህም ስራዎች አንዱ ችግሮችን በራስ አቅም መፍታት እንዲቻል የክልሉ ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ሴቶችን በግብርና ስራ በስፋት ማሳተፍ ይገኝበታል።

በሌሎች ክልሎች ባልተለመደ መልኩ፤ ሴቶች በግብርና ስራ በስፋት ተሰማርተው ተመልክተናል።ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ 10 ሄክታር መሬት ከክልሉ በመውሰድ የበቆሎ ሰብል በመዝራት ሴቶች የምርቱ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ይገኛሉ። ለዛሬ በሴቶች ገጽ በዚህ እና በሌሎች የክልሉን ሴቶች ለማብቃት በሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ የክልሉ ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ የሆኑትን ወይዘሮ ክሪምስ ሴሮ፤ ጋር የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ቆይታ አድርጓል።

ወይዘሮ ክሪምስ እንደሚሉት፤ በክልሉ በኢኮኖሚ እና ከፖለቲካ ተሳትፎ አንጻር የሚነሱ ችግሮች አሉ።በወጣው የ10 ዓመት እቅድ መሰረት ሴቶችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ከማድረግ፣ ከጥቃት ከመከላከል እና ተሳትፏቸውን ከማሳደግ አንጻር ክፍተቶች ተለይተዋል።በተለይም ሴቶች በኢኮኖሞ ረገድ በርካታ ውስንነቶች አሉባቸው።ይህንንም ለመቅረፍ ግብርና እንደ አንድ አማራጭ ተወስዷል፡፡

በክልሉ በግብርና ስራ ሴቶችን ተጠቃሚ ከማድረግ አረገድ ስራዎች እየተሰሩ ነው። በዚህም በግብርና ስራ የተሰማሩ ሴቶችን፣ አቅም የማጎልበት ስራ ይሰራል።በኢኮኖሚ ረገድ ለሴቶች የስራ ክህሎት ስልጠና እየተሰጠ ብድር እየተመቻቸ ነው።ሌላ ደግሞ ሴቶች በእርሻ ስራ ተሰማርተው የተለያዩ የእህል አይነቶች እንዲያመርቱ እና ትራክተር፣ ምርጥ ዘር እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች በቅድሚያ እንዲያገኙ በማድረግ አቅማቸውን የመደገፍ ስራ እየተሰራ መሆኑን ያነሳሉ።

በግብርና ላይ ለተሰማሩ ሴቶች በግብርና ቢሮ ከሜካናይዜሽን ጋር በመነጋገር ትራክተር የመጠቀም እድል በቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጓል።በዚህም 10 ሄክታር መሬት ተከልሎ ሴቶች አምርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው፡፡

ይህን ስራ መስራት የተፈለገው ከልመናም ለመውጣት ታስቦ ነው።በዙ ግዜ በክልሉ በግጭት ምክንያት ሰዎች ይፈናቀላሉ፤ በየዓመቱ ክረምት በመጣ ቁጥር የጎርፍ አደጋ ያጋጥማል።በዚህ ደግሞ ዋነኛ ተጎጂዎቹ ሴቶች ናቸው።እነሱን ለመደገፍ ሁልግዜ ሌሎች አካላት ድጋፍ እንዲያደርጉ ይለመናል።ከዚህ ለመውጣት ከተረጂነት ወደ አምራችነት የሚለውን መርህ በመከተል፤ እራሳቸው አርሰው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

«10 ሄክታር መሬት ላይ በቆሎ የተዘራው ለሙከራ ያህል ነው፤ የፈለግነውን ያህል መሬት እንድን ወስድ ፈቃድ ተሰጥቶናል » የሚሉት ኃላፊዋ፤ የተዘራውም በቆሎ እየደረሰ እንደሆ ይናገራሉ፡፡

ወይዘሮ ክሪምስ ብድር የተመቻቸላቸው ሴቶች፤ አብዛኛዎቹ ጥቃት የደረሰባቸው፣ ያለእድሜ ጋብቻ ምክንያት ትምህርታቸውን ላቋረጡ እና ከቤተሰብ የተገለሉ ሴቶች ወደ ቢሮ ሲመጡ መረጃቸውን በማደራጀት የስራ ክህሎት ስልጠና በመስጠት ወደ ስራ እንዲገቡ እንደተደረገ ያስረዳሉ፡፡

ያለእድሜ ጋብቻ ሊፈጽሙ የነበሩትን ሴቶች ጋብቻውን በሚቃወሙበት ወቅት፤ ከቤተሰብ ሴቶችን የሚያገልበት ሁኔታ አለ የሚሉት ኃላፊዋ፤ አንዳንዴ ቤተሰብ ከቤተሰብ ጋር ባለው ወዳጅነት ሴት ልጃቸው ሳትፈቅድ በራሳቸው ተነሳሽነት ለጋብቻ የሚያመቻቹበት ሁኔታ አለ።ያቺ ልጅ ጋብቻውን አልፈልግም ብላ ከቤተሰብ ስትወጣ የምትጠጋው ዘመድ ስለማይኖራት ለኢኮኖሚ ችግር ትጋለጣለች ይላሉ።ይህንንም ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ ድጋፎች እየተደረጉ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በዚህም የስራ ቦታ፣ መነሻ የሚሆን ብር በብድር መልክ ድጋፍ ይደረጋል።አብዛኛዎቹ ድጋፍ የተደረገላቸው ሴቶች እንደዚህ አይነት ችግር ያጋጠማቸው እና ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ናቸው።



ወይዘሮ ክሪምስ ሴሮ

ወይዘሮ ክሪምስ እንደሚናገሩት ለሴቶች የሚደረገው ድጋፍ፤ ከከተማ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ቦታ የማመቻቸት እና ከብድር ተቋማት ደግሞ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ እና በስድስት ወር የእፎይታ ግዜ መክፈል የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቷል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከቤተሰብ የመገለል እና የጥቃት ችግር ያጋጠማቸው 76 ሴቶች ስራ እንዲጀምሩ መደረጉን በመግለጽ፤ በጉሊት ንግድ፤ በዶሮ እርባታ እና በፍየል እርባታ ላይ እንዲሰማሩ መደረጉን ይናገራሉ፡፡

አብዛኛው እኛ አካባቢ ያሉ ሴቶች ስለመብታቸው ብዙም አያውቁም።ከትዳራቸው ሲፋቱ፣ ጫና ሲደረግባቸው ለመብታቸው ለመከራከር አይሞክሩም።ነገር ግን የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ሁኔታውን ሲደርስበት ለሴቶች ጠበቃ በነጻ እንዲቆምላቸው ይደረጋል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ከንግድ ስራ ጋር ተያይዞ ውጤታማ ሴቶችን የማበረታታትና ለሌለችም ምሳሌ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው፡፡« አንዳንዴ ችግር ገጥሟቸው ሴቶች ለማመልከት ሲመጡ ማመልከቻ ሳይዙ ነው የሚመጡት።ወደ ቢሮው መጥተው በማመልከቻ እንዲያስገቡ ሲነገራቸው፤ ለማጻፍ ብር የለኝም ነው የሚሉት።በዛን ወቅት ባለሙያ ተመድቦ በነጻ ማመልከቻ እንዲጻፍላት ይደረጋል » ሲሉ ይናገራሉ።

ወይዘሮ ክሪምስ አክለውም ጥቃት የደረሰባት ሴት ማመልከቻ አጽፋ እንድትመጣ ከተገደደች ማመልከቻውን ለማጻፍ ገንዘብ ስለሌላት የደረሰባትን በደል ተቀብላ ወደ ቤቷ ነው የምትገባበት ግዜ አለ።ያ እንዳይሆን በማሰብ ቢሮ ውስጥ በነጻ ማመልከቻ የሚጻፍላቸው ሰው እንዲመቻች መደረጉን ያስረዳሉ፡፡

የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ለማጎልበት ከትምህርት ሴክተር ጋር በመሆን፤ የግንዛቤ ስራ እንደሚሰሩ የተናገሩት ወይዘሮ ክሪምስ፤ የሴቶች ተሳትፎ ምን ያህል እንደሆነ ክትትል ይደረጋል።ይህን ስራ በቅርበት የምትከታተል ዳይሬክተር በቦታው ተመድባለች ሲሉ ይናገራሉ፡፡

ኃላፊዋ እንደሚገልጹት፤ በክልሉ ከእናቶች ጤና ጋር ተያይዞ የአንድ መስኮት አገልግሎቶች ላይ የእርግዝና፣ የቤተሰብ እቅድ እና ሌሎች የሴቶች ጤናን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ክትትል እንደሚደረግም ያስረዳሉ፡፡

በክልሉ የአንድ ማእከል ጤና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ተቋማት ሶስት መሆናቸውን በመግለጽ፤ በክልሉ ሶስት ዞንና አንድ ልዩ ወረዳ አለ።በሶስቱ ዞኖች ማእከሎች ያለ ሲሆን በቅርብ ግዜ ውስጥም ተመርቀው ወደ ስራ የሚገቡም አሉ ይላሉ፡፡

**በሌሎች ክልሎች ባልተለመደ መልኩ፤ ሴቶች በግብርና ስራ በስፋት ተሰማርተው ተመልክተናል።ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ 10 ሄክታር መሬት ከክልሉ በመውሰድ የበቆሎ ሰብል በመዝራት ሴቶች የምርቱ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ይገኛሉ**

ኃላፊዋ እንደሚናገሩት ቢሮ የሚሰራቸው 15 ኩነቶች አሉ።በእነዚህ መሰረት፤ የሴቶችን ጥቃት ለመከላከል፤ እስከ ቀበሌ ድረስ ባለው መዋቅር የንቅናቄ ስራ የሚሰራበት ሁኔታ አለ።የንቅናቄ ስራው ብዙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን እንድናገኝ እድል ይፈጥርልናል።አሁን ላይ ለታዳጊ ሴቶች በእምነት ተቋማትና በትምህርት ቤት አማካኝነት የሕይወት ክህሎት ስልጠና መስጠት መጀመሩን ይገልጻሉ፡፡

«ለሕይወት ክህሎት ለስልጠናው የተዘጋጁ መመሪያዎች አሉ።እነዚህን መመሪያዎች በክልሉ ሁለት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች እንዲተረጎም ተደርጓል።በተጠናቀቀው በጀት ዓመትም 700 ሴቶች ስልጠናውን ወስደዋል »ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የተተረጎመው የሕይወት ክህሎት መጻፍ እና ስልጠናዎች ማኅበረሰቡ የስልጠናውን አስፈላጊነት እስኪረዳው ድረስ በቢሮ አማካኝነት የሻይ ቡና መርሃግብር እየተዘጋጀ እታች ወዳለው መዋቅር እንዲዳረስ እየተደረገ ነው።በሌላ በኩል ደግሞ ለሴት ተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያዎች የማቅረብ እና ከመደበኛ ሰዓት ውጭ የማጠናከሪያ ትምህርት እንዲያገኙ መደረጉንም ያነሳሉ፡፡

አሁን ላይ በአካባቢው ያሉ ሴቶች ንቃታቸው እያደገ ይገኛል።በየዓመቱም የበለጠ እየተሻሻለ ነው የሚሉት ወይዘሮ ክሪምስ፤ በርካታ ሴቶች ለራሳቸው መብት መከራከር ጀምረዋል።የመብት ጥሰት ሲያጋጥማቸውም መብታቸውን ለማስከበር ወደ ሕግ አካላት የሚመጡ ሴቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ይናገራሉ።

«በቁጥር ደረጃ መግለጽ ባቻልም፤ በደል ሲደርስባቸው ወደ ሕግ አካላት የሚመጡ ሴቶች ቁጥር ጨምሯል »ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ሰቶች ወደ አመራርነት እንዲመጡ ቀድሚያ መሰራት ያለበት ሴቶች ላይ በመሆኑ፤ ለሴቶች የግንዛቤ ትምህርት ይሰጣል።ሌላው ወደ አመራርነት ለመምጣት እንዳይፈሩ በራሳቸው እንዲተማመኑ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት እንዲሰለጥኑ ይደረጋል።ከሰለጠኑ በኋላ መስከ በመላክ የሰለጠኑትን ስልጠና ተግባራዊ እንዲያደርጉ በማድረግ የአቅም ፍተሻ እንደሚደረግም ያስረዳሉ፡፡

ወይዘሮ ክሪምስ እንደሚሉት ከዚህ በፊት በክልሉ አንድ ቦታ ላይ ብቻ ነበር የአመራርነት ድርሻ ለሴቶች የሚሰጠው።እሱም የማይቀር ስለሆነ ብቻ ሴቶች ጉዳይ ላይ ሴቶች ይሾማሉ።ከለውጡ ወዲህ የሴቶች የአመራርነት ተሳትፎ እያደገ መጥቷል።በክልሉ አሁን አራት ከፍተኛ የሴት አመራሮች ተመርጠዋል።የክልሉ ምክር ቤት አፈጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤ ሴቶች ናቸው።በተጨማሪም በተለያዩ ቢሮዎች በምክትል ደረጃ የሚሰሩ እና ብቃት ያላቸው ሴቶች እየተፈጠሩ ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በፊት በክልሉ ብቸኛ ሴት አመራር፣ አሁን ላይ የጋምቤላ ክልል ፕሬዚዳንት የሆኑት ወይዘሮ ዓለሚቱ ኡሙድ ብቻ ነበሩ።እሳቸው በአመራርነት በነበሩበት ወቅት ሴቶች ወደ አመራርነት እንዲመጡ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል በማለት ይናገራሉ፡፡

በዚህም በሌሎች ክልሎች የሌለ የስራ መዋቅር በክልሉ ተፍጥራል።ይህም በአጠቃላይ የሴክተር መስሪያ ቤቶች የስራት ጾታ ዳይሬክቶሬት የሚል ነው።ይህም በየሴክተሩ በተቻለ መጠን ሴቶች የስራ ኃላፊነት እንዲወስዱ የሚያስችል ነው።ይህም ሴቶች በሹመት መልክ ወደ አመራርነት እንዲመጡ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በስራት ጾታ ዳይሬክቶሬት ላይ የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ሴቶች ወደ ከፍተኛ ቦታ እንዲመጡ፣ ቦታው ላይ ሆነው ያስመዘገቡት ውጤት ይገመገማል።በዛ ቦታ ላይ ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ሴቶች፤ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ዳይሬክተር እንዲሆኑ ይደረጋሉ የሚሉት ወይዘሮ ክሪምስ፣ እሳቸውም በዚህ ሂደት ከስራት ጾታ ዳይሬክተርነት ወደ ሴቶች ቢሮ ኃላፊነት መምጣታቸውን ይገልጻሉ፡፡

ወይዘሮ ዓለሚቱ የክልል ፕሬዚዳንት መሆናቸው ለሴቶች ትልቅ መነቃቃት የሚፈጥር ነው የሚሉት ወይዘሮ ክሪምስ ሴቶች የክልል እርሰ መስተዳደር ሲሆኑ በኢትዮጵያ ደረጃም ያልተለመደ ነው። ይህ ለበርካታ ሴቶች የይቻላል መንፈስ የሚያጭር ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የክልሉ ሴቶች በመንግስት በኩል የሚደረግላቸው ድጋፍ እና የማጠናከሪያ ስልጠና እንዳለ ሆኖ፤ ሴቶች እራሳቸው ለማብቃት ራሳቸውን ለማሳደግ ጥረት እንዲያደርጉ የሚመከሩት ኃላፊዋ፤ ሴቶች የቁጠባ ባህላቸው ሊዳብር፣ በራስ የመተማመን አቅማቸው እንዲጎለበት ሊሰሩ ይገባል ይላሉ።በሌላ በኩል የዜግነት ግዴታም ስለሆነ፣ ለቀጣይም ይህን አድርጌያለው ብሎ በኩራት ለማውራት በበጎ ፈቃድ ስራዎች ሊሳተፉ ይገባል ሲሉ መልክታቸውን ያስተላልፋሉ።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ግርማ መንግሥቴ

ሁኔታዎችን፣ ኩነቶችን፣ ታሪክንና አጠቃላይ እንቅስቃሴዎችን እለት በእለት፣ እግር በእግር ሲሰንድ የኖረው፤ ጎምቱው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ያላነሳቸውን ነገሮች ከመዳሰስ ይልቅ "ምን የቀረው ነገር አለና" የሚለውን በመያዝ አንዳንድ አስተናግዷቸው የነበሩ ጉዳዮችን ማንሳቱ ይበጃል።

የዛሬዎቹ ምርጫዎቻችን ከየዘርፎቹ ናቸው። በየራሳቸው የቆሙ እንጂ በታሪክ አንዱ ከሌላው የተሳሰሩ አይደሉም። በወቅቱ የተከናወኑ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን ትኩረት ያደረጉ ናቸው። እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል።

### የፖርቱጋል ጋዜጣ ስመነን መጽሔት

የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች በተለይ ስለ እኛ ሀገር የበለጠ በማስረዳት ሰፊ ሐተታ በመስጠት ላይ ናቸው።

የታወቀ ባለ ሥዕል የመነን መጽሔት በአዲስ አበባ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ይታተማል፤ በመጨረሻውም ክፍል እትሙ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ኦፊሴዬላዊ ጉብኝት መሠረት በማድረግ የዛሬይቱ ፖርቱጋል ከደረሰችበት ደረጃ በፊት የነበረችበትን ታሪካዊ ሁኔታ ከፍ ባለ አስተያየት ያለ ፖለቲካ ስሜት መጽሔቱ ሰፊ አርቲክል አውጥቷል።

መጽሔቱ በኢትዮጵያና በፖርቱጋል መካከል ያለውን ብዙ መቶ ዓመታት የቆየውን የወዳጅነት ግንኙነት ከዛሬው የአፍሪካ ምርመራ ጋር የተያያዘውን የነገሥታቶቻችንንና የባሕር መሪዎቻችንን ተግባሮች ከገለፀ በኋላ በፖርቱጋል መንግሥት በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ጊዜ የነበረውን አቋምና የላይቤሪያን አገሮች ጀርመኖች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳይወሩ የተደረገውን የፖለቲካ ትግል ይገልፃል። የፖርቱጋል መንግሥት የአዞር ደሴቶችን የተባበሩት መንግሥታት የጦር ሰፈር እንዲሆን መፍቀዱ በጣም ጠቃሚ ሆኗል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ካስረዳ በኋላ መነን መጽሔት ፖርቱጋል ምን እንደ ሆነች ለወዳጅዋ ኢትዮጵያ ለማስገንዘብ በእርሻ፣ በኢንዱስትሪና በኢኮኖሚ ረገድ የተደረገውን መሻሻል ገልጿል።

በዚህ ከሚገባ አርቲክል ጋር ጎን ለጎን ሆነው የፖርቱጋል ፕሬዚዳንት የአንዳንዶች ሐውልቶቻችንን የአዲሲቷ ሊስቦን ሕንፃዎችና ያለፉት የሁለት ዓመታት ሕንፃዎችና የኢንዱስትሪ ውጤቶች አስረጂ ፎቶግራፎች ታትመው ወጥተዋል።

**(አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ዓርብ ነሐሴ 1 ቀን 1951 ዓ.ም)**

### አፍሪካውያን መምህራን

<u>ዋሽንግተን</u>:- ስድስት አፍሪካውያን መምህራን በዛሬው ዘመን የአፍሪቃን አሕጉር የገጠማቸው የትምህርት አሰጣጥ ችግር የሠለጡኑ መምህራን ማነስ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እነዚህ መምህራን በዓለም ትምህርት አሰጣጥ ሙያ ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት ለጋዜጠኞች በተደረገው ጉባኤ ላይ የየራሳቸውን አገር የትምህርት አሰጣጥ ችግር አብራርተው ገልፀዋል። እነዚህም መምህራን በዚህ ሳምንት ውስጥ የትምህርትን ችግር የሚያጠና ቋሚ ኮሚሲዮን ለመመሥረት ጉባኤ በማድረግ ላይ የሚገኘው 24 ሰዎች የሚገኙበት ኮሚቴ አባሎች ናቸው።

ለቀረቡለት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ 50,000 አባላት የሚገኙበት የናይጄሪያ የመምህራን ኅብረት ዋና ጸሐፊ የሆነውና የኮሚቴው ሊቀመንበር አዲሱ የአፍሪቃ ኮሚሲዮን በጥር 1960 ዓ/ም የመቋቋሙ ክንውን እንዳለቀ የመምህራን እጥረትን ችግር [የ]ማቃለል [ሥራ] ይጀመራል ሲል ተናግሯል።

ኮሚሲዮኑ እንደ አማካሪ ሆኖ በማገልገል ከመንግሥቱ ጋር መምህራንን በማዘጋጀት በኩል ይረዳል የተባለውን ችግር በፍጥነት የሚያቃልል ይሆናል ሲል ጨምሮ ገልጿል።

የኢትዮጵያ መምህራን ኅብረት ሊቀመንበር የሆኑት አቶ እሸቴ ባዩ ስለ ኢትዮጵያ ሲናገሩ መንግሥታቸው የመምህራንን ቁጥር ለመጨመር በትጋት በመሥራት ላይ መገኘቱን ገልፀው ንግግራቸውንም በመቀጠል ምንም እንኳን ችግሩ ሊወገድ የሚችል ባይሆን ቅሉ በመምህርነት የሠለጡኑ ወጣቶች ብዛት በየዓመቱ እየጨመረ መሄዱን አላቋረጠም ሲሉ አስረድተዋል። ከዚህም በማያያዝ ይህንንም ተግባር በትጋት እንዲከናወን ያደረገው መምህራንን ከፍ ባለ ዋጋ ከውጭ አገር እየቀጠሩ ሚምጣት ያሳየው ጉዳት ነው ሲሉ ጨምረው ገልፀዋል።

**(አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ቅዳሜ ሐምሴ 30 ቀን 1951 ዓ.ም)**

### በወ.ወ.ክ.ማ የሚደረግ ንግግር

ነሐሴ 9 ቀን 1951 ዓ/ም ከምሽቱ 1 ሰዓት አቶ ዮሐንስ ወልደ ገሪማ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የጤና ጥበቃና የሕዝብ አገልግሎት ዲሬክተር "የሕዝብ አገልግሎት" በሚል አርዕስት በወጣቶች ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር አዳራሽ ንግግር ስለሚያደርጉ ማንኛውም ሰው ንግግሩን ሊያዳምጥ ይችላል።

**(አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ነሐሴ 8 ቀን 1951 ዓ.ም)**

### በትምህርት ረገድ ልዩነት ማድረግ ያራርቃል

ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ ሚስተር ሲ ኤስ ጃ የሕንድ ዋና መልዕክተኛ በአንዳንድ የእንግሊዝ ግዛቶችና በሌሎች ጥገኞች ግዛቶች በትምህርት ረገድ የሚደረገውን የዘር ልዩነት ተቃውመዋል። ሚስተር ጃ በትምህርት የሚደረግ የዘር ልዩነት "የዘር ክፍያን ምግባር የሚደግፍ ስለሆነ እንዲህ ያለውን አለመግባባት የሚያባብስ ነው" ብለዋል።

ራሳቸውን ከማይገዙ ግዛቶች የደረሳቸውን ዜና ለኮሚቴው በመግለፅ ማንኛውም ዘር ከሌላው ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር የቀረበ አለመሆኑንና ማንኛውም ዘር ከሌላው የበታችነት የሌለበት መሆኑን ታሪክ ይነግረናል።

"ነገር ግን በኮንጎ፣ በመካከል አፍሪካ፣ በኬንያ፣ በዩጋንዳና በሌሎች በብዙ ግዛቶች ትምህርት የዘር ልዩነት እየተደረገ ይሰጣል" ብለዋል።

የሠለጠነና የተሻለ ትምህርት ለፖለቲካ ርምጃና ለራስ አገዛዝ ይጠቅማል በማለት በትምህርትና በፖለቲካ ኃላፊነት መካከል የጋራ ግንኙነት እንዲኖር ያሻል ብለዋል።

ስለተገዥዎቹ አገሮች ርምጃ በጠቅላላ አስተያየት በመስጠት በኦስትራሊያ ስር የምትተዳደረዋ ፖፑአ ያደረገችው መሻሻል ከፍ ያለ መሆኑንና፣ ኒው ዚላንድ በኩክ፣ በኒኡና ቶኮሎ ደሴቶች ትምህርትን ለማስፋፋት ባደረገችው ጥረት ሕንድ የተደሰተች መሆኑን አስገንዝበዋል።

ሕንድ ቤልጂክ ወደ ኮሚቴው መልዕክተኛ አለመላክዋን በማሳሰብ ፖርቱጋል በርስዋ ስር የሚተዳደሩት አንጎላ፣ ሞዛምቢክ እንዲሁም አነስተኛ የሆኑ የፖርቱጋል ግዛቶችን ከቁምነገር አለመቁጠርዋ በዘመናችን ከሚያሳዝኑት ጉዳዮች አንዱ ነው ብለዋል።

ንግግራቸውን በመቀጠልም፣ እነዚህ ግዛቶች የገዥው ሀገር ክፍል ናቸው ተብሎ ቢወራም፣ በእርግጥ የቅኝ አገር መሆናቸው ጥርጥር እንደ የሌለው በመግለፅ፤ እነዚህ በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማለቂያ ክፍል የኮሎኒያሊዝምን (የቅኝ አገዛዝን) ቀንበር የተሸከሙት ሕዝቦች ኃዘን ተካፋይ መሆናችንን እንገልፃለን ብለዋል።

**(አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ሚያዝያ 28 ቀን 1951 ዓ/ም)**

# ዓለም አቀፍ

## ትራምፕ በመጪው ምርጫ ከተሸነፉ ዳግም ለፕሬዚዳንትነት እንደማይወዳደሩ ጠቆሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

<u>አዲስ አበባ</u>:- የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንትና የአሁኑ የካማላ ሐሪስ ተፎካካሪ ዶናልድ ጄ ትራምፕ በመጪው ምርጫ ካላሸነፉ በፈረንጆቹ 2028 እንደማይወዳደሩ ጠቆሙ።

የ78 ዓመቱ የዕድሜ ባለፀጋ ትራምፕ ላለፉት ሦስት ተከታታይ የፕሬዚዳንታዊ ምርጫዎች ሪፐብሊካንን ወክለዋል።

በቅርቡ ባደረጉት አንድ ቃለምልልስ በቀጣይ ምርጫ በካማላ ሐሪስ ከተሸነፉ ከ4 ዓመት በኋላ ዳግም ይወዳደራሉ ወይ ተብለው ሲጠየቁ፣ "አይመስለኝም። አላደርገውም" ብለዋል። ይሁንና መጪውን ምርጫ እንደሚያሸንፉ በጽኑ ተስፋ አድርገዋል።

የአሜሪካ ሕግ አንድ ፕሬዚዳንት ከሁለት የሥልጣን ዘመን በላይ በዋይት ሐውስ መቆየትን ይከለክላል። ይህም ማለት ትራምፕ መጪውን ምርጫ ቢያሸንፉ እንኳ በ2028 በድጋሚ ለፕሬዚዳንትነት መወዳደር አይችሉም።

ባለፈው ሐሙስ በአይሁድ-እሥራኤላውያን ካውንስል ጉባኤ ላይ የተገኙት ትራምፕ "ከተሸነፍኩ አንዱ ምክንያት እናንተ ናችሁ" ሲሉ ተናግረዋል።

"ለመሆኑ እኔ ከተሸነፍኩ ምን ዓይነት መዓት ሊወርድ እንደሚችል ያውቃሉን?" ሲሉ ወደ ካማላ ሐሪስ ያዘነበሉ አይሁድ-አሜሪካውያንን ወቅሰዋል።

ይህ አስተያየታቸው በካማላ ሐሪስ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን እና በገለልተኛ አይሁድ መራጮች ዘንድ ቅሬታን አሳድሯል።

ከዚህ ቀደም ትራምፕ የመሸነፍ ዕጣ ሊገጥማቸው እንደሚችል የሚጠቁም ንግግር ከአንደበታቸው ወጥቶ አያውቅም። ያለፈው ምርጫም ተጭበርብሮ ነው እንጂ አሸናፊው ጆ ባይደን ሳይሆኑ እኔ ነኝ ሲሉ ይከራከራሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ትራምፕ መሸነፍም እንዳለ የገባቸው ይመስላል።



የፖለቲካ ተንታኞች ይህ የትራምፕ አስተያየት ከጆ ባይደን ገለል ማለት ወዲህ የመጣ አዲስ አመል ነው ይላሉ። በተለይም ካማላ ሐሪስ ከፍተኛ ተቀናቃኛቸው እንደሆኑ በመረዳታቸው እንደሆነ ይገምታሉ።

ካማላ ሐሪስ ጆ ባይደንን ከተኩ ወዲህ በዲሞክራቶች ዘንድ ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ መነቃቃት ተፈጥሯል።

በታኅሣሥ ወር ብቻ በምርጫ ቅስቀሳ ካማላ ሐሪስ 190 ሚሊዮን ዶላር መሰብሰብ የቻሉ ሲሆን ትራምፕ ግን 130 ሚሊዮን ብቻ ነው ማሰባሰብ የቻሉት።

ባለፈው እሑድ በተሰበሰበ የሕዝብ አስተያየት ሐሪስ ዶናልድ ትራምፕን 52% ለ48% እየመሩ እንደሆነ ተመላክቷል። ወሳኝ በሚባሉት ግዛቶች ግን ዶናልድ ትራምፕ እየመሩ ነው። ይሁንና ቀድሞ ይመሩበት ከነበረው ነጥብ ልዩነቱ እየጠበበ መጥቷል።

የቢቢሲ የአሜሪካ አጋር የሆነው ሲቢኤስ በሠራው የሕዝብ አስተያየት ቀመር በወሳኝ ግዛቶች ትራምፕ 51% ለ49% እየመሩ ነው። ኤንቢሲ ትናንት ይፋ ባደረገው ሌላ የሕዝብ አስተያየት ቀመር ደግሞ ሐሪስ ትራምፕን በ5 ነጥብ እየመሩ ነው።

48% የሚሆኑ ድምፅ ለመስጠት የተመዘገቡ መራጮች ካማላ ሐሪስን በበጎ ማየት እንደጀመሩ አንድ ጥናት አመላክቷል።

ይህ የሕዝብ አስተያየት መራጮች በስደተኞች ጉዳይ፣ በምጣኔ ሃብት ጉዳይ እና በኑሮ መወደድ ጉዳይ ልባቸው ወደ ትራምፕ ያጋደለ እንደሆነ አሳይቷል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## ሄዝቦላህ የሚቃጣበትን "የትኛውንም እርምጃ ለመመከት ዝግጁ" መሆኑን አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሂዝቦላህ የሚቃጣበትን ማንኛውንም ርምጃ ለመመከት ዝግጁ መሆኑን አስታወቀ። እሥራኤል እና ሄዝቦላህ ድንበር አካባቢ የሚያደርጉትን የተኩስ ልውውጥ አጠናክሮ እንደሚቀጥልም አስታውቋል። ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ደግሞ ሁለቱ ወገኖች ከለየለት ጦርነት እንዲቆጠቡ እያሳሰበ ይገኛል።

የእሥራኤል ጦር ኃይል እንዳለው ቅዳሜ ምሽት እና እሑድ ንጋት 150 ሮኬቶች፣ ሚሳዔሎች እና ሌሎች የጦር መሣሪያዎች ወደ እሥራኤል ተተኩሰዋል።

አንዳንድ ጥቃቶች ከዚህ ቀደም ከሚመቱት ዒላማ ዘልቀው በመውደቃቸው በሺዎች የሚቆጠሩ እሥራኤላውያን ከቦምብ አደጋ ለመከላከል በተሠሩ መጠለያዎች ውስጥ ተሸሽገው እንደነበር ተሰምቷል። አብዛኛዎቹ ጥቃቶች የደረሱት ሀይፋ ከተማ አቅራቢያ ነው።

እሥራኤል በአፀፋው በደቡባዊ ሊባኖስ በወሰደችው እርምጃ በሺዎች የሚቆጠሩ የሄዝቦላህ ሮኬት ማስወንጨፊያዎችን አውድሜያለሁ ብላለች።

እሑድ ንግግር ያሰሙት የእሥራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤኒያሚን ኔታኒያሁ ሀገራቸው "ፀጥታዋን ለማስከበር የትኛውንም ዓይነት እርምጃ ትወስዳለች" ብለዋል።

"ሄዝቦላህ ላይ ሊታሰብ የማይችል ኪሳራ አድርሰናል" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስራኤል-ሊባኖስ ድንበር ያሉ እሥራኤላውያንን ወደ ቀያቸው ለመመለስ ቃል ገብተዋል።

የሄዝቦላህ ምክትል መሪ የሆኑት ናይም ቃሲም በበኩላቸው "ማስፈራራቶች አያግዱንም። የትኛውንም ወታደራዊ እርምጃ ለመመከት ዝግጁ ነን" ሲሉ ተደምጠዋል።

እስራኤል ባለፈው ዓርብ በሊባኖስ ዋና ከተማ ቤይሩት በፈፀመችው ጥቃት ምክንያት የተገደሉት የሄዝቦላህ ከፍተኛ ኃላፊ የሆኑት ኢብራሒም አቂል ቀብራቸው ተካሂዷል። በቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት ቃሲም "አሁን አዲስ ምዕራፍ ላይ ነን። በግልፅ [ከእስራኤል ጋር] ተፋጠናል" የሚል ንግግር አሰምተዋል።

ሼኽ ናይም ቃሲም ለቡድኑ አባላት ባስተላለፉት መልዕክት እሥራኤል ዒላማዎቿን እየሳተች ነው ብለው ነገር ግን ሄዝቦላህ ባለፉት ሦስት ቀናት ጥቃት ማድረስ መቀጠሉን ገልፀዋል።

አክለውም በሚቀጥሉት ቀናት በሰሜናዊ ሊባኖስ የሚኖሩ በርካታ የእሥራኤል ነዋሪዎች ከመኖሪያቸው እንደሚፈናቀሉ እና እሥራኤል የቡድኑን ጥንካሬ መቋቋም እንዳቃታት ተናግረዋል።

ሄዝቦላህ የሐማስ አጋር ሲሆን ሐማስ ደግሞ ኢራን "አክሲስ ኦፍ ሬዚዝስታንስ" እያለች የምትጠራው ጥምር ቡድን አባል ነው።

የኢብራሒም አቂልን ቀብር ለመታደም በርካታ ቁጥር ያለው ሰው አደባባይ የወጣ ሲሆን የሄዝቦላህ አባላት የሆኑ ሰዎች "ሞት ለአሜሪካ" የሚሉ እና ሌሎች የተቃውሞ ድምፆችን ሲያሰሙ ነበር።

የሊባኖስ ባለሥልጣናት በተደረገ ጥቃት ኢብራሒም አቂልን እና 15 አብረዋቸው የነበሩ የሄዝቦላህ አባላትን ጨምሮ 45 ሰዎች መገደላቸውን አስታውቀዋል። ዘገባው የቢቢሲ ነው፡፡

Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ዘመን
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ድረገጽ፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ማክሰኞ ስፖርት


ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውጤታማ የሆኑባቸው የሳምንቱ መጨረሻ ውድድሮች

**ብርሃን ፈይሳ**

በተለያዩ ዓለማት በሳምንቱ መጨረሻ በተካሄዱ የአትሌቲክስ ውድድሮች በርካታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውጤታማ ሆነዋል።ይህ ወቅት እንደ ኦሊምፒክ እንዲሁም ዳይመንድ ሊግ ያሉ ውድድሮች የሚጠናቀቁበት እንደመሆኑ በተለያዩ ከተሞች የጎዳና እና የመም ውድድሮች በስፋት የሚከናወኑበት ነው።ባለፈው ሳምንት መጨረሻ በተካሄዱት የሩጫ ውድድሮችም በተለያዩ ርቀቶች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውጤታማ መሆን ችለዋል።

ከእነዚህ ውድድሮች መካከል አንዱ በአምስተርዳም የተከናወነው የ10 ማይል የጎዳና ላይ ሩጫ ሲሆን፤ በቀድሞው የዓለም ቻምፒዮና ሙክታር እድሪስ አሸናፊነት ተጠናቋል።ሙክታር በ2017 የለንደን እንዲሁም በ2019 የዶሃ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና መድረኮች በ5ሺ ሜትር በተከታታይ አሸናፊ በመሆን በእንግሊዛዊው አትሌት ሞሃመድ ፋራህ ተይዞ የነበረውን የርቀቱን የበላይነት ወደ ሃገሩ የመለስ ጀግና አትሌት መሆኑ ይታወቃል።ይሁንና አትሌቱ በተደጋጋሚ በሚገጥመው ጉዳት ምክንያት ያለውን ብቃት እንደ ኦሊምፒክ ባሉት መድረኮች አውጥቶ ማሳየት አልቻለም።እአአ በ2022 በኦሬገኑ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ድልን በተደጋጋሚ በተቀዳጀበት ርቀት ሃገሩን ወክሎ ቢሰለፍም ውጤታማ ሊሆን አልቻለም።ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት በውድድሮች ላይ እምብዛም ያልታየው ሙክታር አምስተርዳም ላይ በድል ብቅ ብሏል።ይህም አትሌቱ ፊቱን ከመም ወደ ጎዳና ላይ ውድድሮች ማዞሩን የሚያመላክት ነው።



**ሙክታር እድሪስ በአምስተርዳም የ10 ማይል የጎዳና ላይ ሩጫ አሸናፊ ሆናል፤**

ፈጣን በነበረው ውድድር ሙክታር ፉክክሩ ከተጀመረ ከተወሰነ ቆይታ በኋላ ተፎካካሪውን በመቅደም በመሪነት እስከመጨረሻው መጓዝ ችሏል።ከዩጋንዳዊው የ10ሺ ሜትር ሶስት ጊዜ ቻምፒዮን ጀሹዋ ቼፕቴጊ ጋር በዚህ ውድድር መገናኘቱ ሩጫው ለሙክታር ሊከብድ እንደሚችልና በመካከላቸውም ከፍተኛ ፉክክር ሊኖር እንደሚችል አስቀድሞ ተገምቶ ነበር።ይሁንና ሙክታር ርቀቱ እየጨመረ ሲሄድ ፍጥነቱንም ይበልጥ እየጨመረ ተፎካካሪውን በ27 ሰከንዶች ቀድሞ ሊያጠናቅቅ ችሏል።የገባበት 45:44 የሆነ ሰዓትም በቦታው ከተመዘገቡት መካከል ከፈጣኖቹ ተርታ ተቀምጧል።ለአሸናፊነት በእጅጉ የተጠበቀው ቼፕቴጊ በበኩሉ 45:18 በሆነ ሰዓት ርቀቱን ሸፍኗል፤ ይህም ሰዓት አትሌቱ ከሶስት ዓመታ በፊት ካስመዘገበው በሶስት ሰከንዶች የዘገየ ነው።

በሴቶች በኩልም በተመሳሳይ ኢትዮጵያዊቷ አትሌት አሳየች አይቼው ኬንያዊቷን አትሌት አስከትላ በመግባት አሸናፊ ሆናለች።በዚህ ውድድር የመሪነቱን ስፍራ ተቆጣጥራ ውድድሩን ስትመራ የቆየችው ግላድየስ ቼፕኩሩይ ብትሆንም አትሌት አሳየች ሳትጠበቅ የመጨረሻውን መስመር በቀዳሚነት መርገጥ ችላለች።ርቀቱን ለመሸፈን የፈጀባት ሰዓት 51:15 ሲሆን፤ ኬንዊቷ ከ19 ሰከንዶች መዘግየት ተከትላ ገብታለች።ሶስተኛ የሆነችው አትሌት ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት መብራት ግደይ 52:14 የሆነ ሰዓት አስመዝግባለች።

በታይዋን በተካሄደው የማራቶን ውድድርም ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሁለቱም ጾታ ተከታትለው በመግባት የውድድሩን የበላይነት ሊቆጣጠሩ ችለዋል።40ሺ ሯጮች በተካፈሉበት በዚህ ማራቶን ደሳለኝ ግርማ፣ ደጀኔ ደበላ እና አሰፋ ተፈራ ከአንድ እስከ ሶስት ያለውን ደረጃ በመያዝ አጠናቀዋል።ጠንካራ ፉክር በታየበት በዚህ ውድድር አትሌቶቹ ለመሸናነፍ ያደረጉት ፉክክር በሰከንዶች ብቻ የተለያየ መሆኑ ለዚህ ማሳያ ነው።በሴቶች መካከል በተካሄደው ውድድርም በተመሳሳይ ከፍተኛ ፉክክር የታየ ሲሆን፤ በሰከንዶች ብቻ ተለያይተው ውድድራቸውን አጠናቀዋል።በዚህም መሰረት ኢትዮጵያዊያኑ ጫልቱ ጪምዴሳ እና ፋንቱ ዘውዱ ተከታትለው ሲገቡ ኬንያዊቷ ሞኒካ ቺቤት ሶስተኛ ደረጃን ይዛለች።

በሄንግሺ ሃይቅ በተደረገው ሌላኛው ማራቶን ደግሞ ኬንያዊው አትሌት በናርድ ኪፕኮሪር ሲያሸንፍ ኢትዮጵያዊው መኳንንት አየነው ሁለተኛውን ደረጃ ሊይዝ ችሏል።ሁለቱ አትሌቶች በአንድ ደቂቃ ተለያይተው የገቡ ሲሆን፤ ከውድድሩ አስቀድሞ ይጠበቅ እንደነበረው በኢትዮጵያውያኑ እና የኬንያ ተቀናቃኞቻቸው መካከል ብርቱ ፉክክር ተደርጓል።ኤርትራዊው አትሌት ብርሃኔ ጸጋይ ደግሞ ሶስተኛው አትሌት ሆኗል።በሴቶች አታለል አንሙት አሸናፊ ስትሆን፤ የሃገሯ ልጅ ደራርቱ ኃይሉ ደግሞ ሶስተኛ ሆናለች።

## ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
### በየሳምንቱ የሚታተም

# የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማሕበራዊ ኃላፊነት ፋይዳ

**በአስምነህ ቸርነት**

ከኅብረት ሥራ ማኅበራት ሰባት መሰረታዊ መርሆዎች መካከል አንዱ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ባጸደቋቸው ፖሊሲዎች አማካኝነት በአካባቢያቸው ላለው ሕብረተሰብ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችል የማኅበራዊ ኃላፊነት ተግባራት ማከናወን ነው። በዚህም መሰረት የሀገራችን ኅብረት ሥራ ማኅበራት በዓመት ከሚያገኙት ትርፍ 5 በመቶ ያህሉን ለማኅበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት በመመደብ የአካባቢና ማኅበራዊ ልማት ላይ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ።

የማኅበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት በሚገኙበት አካባባቢ ላለው ማኅበረሰብ አወንታዊ የልማት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ከማስቻሉ ሌላ እራሳቸውን ለማስተዋወቅና ለቢዝነስ ተግባራቸው ቀጣይነት ጉልህ ጠቀሜታ ያለው ነው። ማኅበራዊ ኃላፊነት ለመወጣት ከሚተገብራቸው ተግባራት መካከል በአካባቢ የማኅበረሰብ ልማት፣ የአካባቢ ብክለት በሚቀንሱ ተግባራት፣ በበጎ አድራጎት ተግባራትና በስራ ዕድል ፈጠራ ተሳትፎ ይጠቀሳሉ።

በዚህም መሰረት በርካታ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በአካባቢ የማኅበረሰብ ልማት ሰፊ ተሳትፎ አላቸው። ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሚያገኙት ትርፍ የአካባቢያቸውን ማኅበራዊ ችግሮች በመለየት የተለያዩ ማኅበራዊ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ለማኅበረሰብ ግንባታ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ማኅበራቱ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ኬላዎች፣ ድልድይና መንገድ በመስራት፣ የመጠጥ ውሃና የመብራት አገልግሎት እንዲገባ በማድረግ ይሳተፋሉ። እንዲሁም ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የራሳቸውን አሻራ በማሳረፍ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ከዚህ በተለየ ሁኔታ በቡና ምርት ግብይት ላይ የሚሳተፉ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በዓለም አቀፍ ፍትሃዊ ንግድ ተሳትፎ በሚያገኙት ተጨማሪ ክፍያ ፕሮጀክቶች በመቅረጽ



በማኅበራዊ ልማት ከፍተኛ ተሳትፎ አላቸው። ለአብነት የኦሮሚያ የቡና ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን የኢትዮጵያ ኦርጋኒክ ቡናን በጥሬው አሸጎ ወደ ውጪ ከመላክ ባሻገር ቡናን ቆልቶና አሸጎ የዋንኮ ቡና በሚል የብራንድ ስያሜ ለዓለም ገበያ እያስተዋወቀ ይገኛል። በዚህም በፕሪሚየም የሚያገኘውን ተጨማሪ ክፍያ ማኅበራቱ በሚገኙበት አካባቢ ተለይተው ለታወቁ ችግሮች ወደ 394 የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ የትምህርት ቤት፣ የጤና ጣቢያ፣ የመንገድ፣ የቡና መሰረተ ልማት የመሳሰሉት ግንባታዎች በማከናወን የቡና አምራች ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል።

ኅብረት ሥራ ማኅበራት የአካባቢ ብክለት በሚቀንሱ ተግባራት እንደዚሁ ተሳትፎ አላቸው። በዚህ ተግባር ታዳሽ ኃይል መጠቀም፣ የደን ልማትና የካርቦን ልቀት መከላከል፣ ተፈጥሯዊ ይዘት የጠበቀ ምርት ማምረት የመሳሰሉት ይካታተላሉ። ኅብረት ሥራ ማኅበራት የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቋቋም በሚደረገው ጥረት በደን ልማትና እንክብካቤ በቀጥታ እየተሳተፉ ይገኛሉ። እነዚህ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ደንን በማልማትና በመጠበቅ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቋቋም አይነተኛና ሚና ያላቸው ናቸው።

የሀገራችን የቡና አምራች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጥራት ያለው ተፈጥሯዊ የሆነ ቡና በማቅረብ ለአካባቢያዊ ብክለት መቀነስ አዎንታዊ ተፅዕኖ በመፍጠር የፌየር ትሬድ (fair trade) ተጨማሪ ክፍያ ተጠቃሚ ናቸው። ከእነዚህ መካከል አንዱ የሆነው የኦሮሚያ የቡና ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን ኦርጋኒክ ቡና ለገበያ ከማቅረቡ ሌላ አርሶ አደሩ በሶላር ታዳሽ ኃይል ተጠቅሞ የመስኖ ውሃን በመሳብ የቡና ምርትና ምርታማነትን እዲያሳድግ በሙከራ ፕሮጀክት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል።

እንዲሁም የቡና ገለባን አርሶ አደሩ እያቃጠለ አካባቢን እንዳይበክል በሱማሌ ክልል የቡና ገለባን ወደ ከሰል የሚቀይር ፕሮጀክት በመጀመር ለወጣቶች የስራ እድል ፈጥሯል። በተጨማሪም ዩኒየኑ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመከላከል በደን ተከላ ካርቦን በመሰብሰብና በመሸጥ የስራ እድል ለአርሶ አደሩ በመፍጠር ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል። በቅርቡ ከወለጋ አካባቢ ብቻ በካርቦን ሽያጭ 23 ሚሊዮን ብር አግኝቷል። በአሁኑ ጊዜ የካርቦን ምርት ፕሮጀክት በጅማ፣ ጉጂ፣ ቡኖ በደሌና ኢሉ አባቦር ዞኖች ተደራሽ በማድረግ ለ277 የአርሶ አደር ቤተሰቦች በተለይም ለሴቶች የስራ እድል መፍጠር ችሏል።

ሌላው ኅብረት ሥራ ማኅበራት ማኅበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የሚያከናውኑት ተግባር የበጎ አድራጎት ተሳትፎ ነው። በዚህ ረገድ ወላጅ ለሌላቸው ልጆች፣ ለአካል ጉዳተኞችና አቅም ለሌላቸው የአርሶ አደር ልጆች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ድጋፍ በማድረግና በማስተማር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እየተወጡ ይገኛሉ። እንዲሁም በሀገራችን በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ለሚደርሱ ቀውሶች ድጋፍ በመስጠት፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት በመጠገንና የፍጆታ ቁሳቁሶች በመደገፍ የኅብረት ስራ የመደጋገፍና የመረዳዳት እሴትና መርሆን ይተገብራሉ።

በሀገራችን በተለይም በከተሞቸ አካባቢ ጎልቶ ከሚታዩ ማኅበራዊ ችግሮች መካከል ሥራ አጥነት ተጠቃሽ ነው። በዚህ ረገድ በስራ ዕድል ፈጠራ አይነተኛ አስተዋጽኦ ካላቸው ዘርፎች መካከል የኅብረት ሥራ ዘርፍ አንዱ ነው። ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተለያዩ የሥራ መስኮች ለዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ፈጥረዋል። በግንባታ ሥራዎች፣ በግብዓት ሥርጭት፣ በግብርና ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች፣ በቢሮ አገልግሎትና በሌሎች ሥራዎች ለሀገራችን ዜጎች ሰፊ የሥራ እድል በመፍጠር ጉልህ ሚና አላቸው።

በተጨማሪም ኅብረት ሥራ ማኅበራት በቁጠባና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ዜጎች ቆጥበው በመበደር የራሳቸውን ቢዝነስ እንዲጀምሩ በማድረግ ለሥራ ዕድል ፈጠራ የማይናቅ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። በእነዚህም የማኅበራዊ ኃላፊነት ተግባራት አባሎቻቸውንና የአካባቢያቸውን ማኅበረሰብ በመጥቀም የመንግስትን ጫናን በማቃለል ትልቅ ድጋፍ ያደርጋሉ።

አድራሻ | የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Ethiopia cooperative Commission | Website: www.fca.gov.et